# መሪው

ጌታ ይባርክህ፡ ወንድም ኔቪል።

ዛሬ ማታ ወደ ቤተክርስቲያን በመመለሴ በጣም ደስተኛ ነኝ። ትንሽ ድምጼ ተይዟል። የዛሬ ጥዋት መልእክት፡ ረዥም ቢሆንም፡ እርግጠኛ ነኝ እዚህ ስለነበር ተባርኬበታለው። እና እኔ እራሴ፡ እሱን በማምጣቴ ተባርኬበታለው፡ እና እሱን በመስማታችሁ እንደተባረካችሁበት ተስፋ አደርጋለሁ። [ጉባኤው፡ “አሜን” አለ።—እርታዒ።]

2 የክርስቶስን አገልጋይ የሚገነቡት፡ እነዚህ ነገሮች መሆናቸውን አትርሱ፡ ሁልጊዜም አስታውሱ። እያችሁ፡ በመጀመሪያ እምነት፡ ቀጥሎም በጎነት ነው። አሁንም አስታውሱ፡ ነገሮች በመንፈስ እስኪሰሩ ድረስ መንፈስ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን መደምደሚያ ራስ አይሆንም። ምንም ብታደርጉ ምንም ማለት አይደለም፡ እያችሁ። የክርስቶስን አካል የሚገነቡት እነዚህ ነገሮች ናቸው፡ እያችሁ፡ እነዚህ ነገሮች። አሁን፡ **እዚህ** ጋር የሚቀድመው፡ እምነታችሁ እንደሆነ፡ ያንን አትርሱ። የክርስቶስ ፍጹም ቁመና እስኪገለጥ ድረስ፡ በጎነት፡ እውቀት፡ እና የመሳሰሉት፡ ይጨመሩበታል፡ ከዚያም መንፈስ ቅዱስ በላዩ ላይ መጥቶ አንድ አካል አድርጎ ያትመዋል። እነዚህ ነገሮች ግዴታ መሆን አለባቸው። ስለዚህም፡ ኢየሱስ “በፍሬያቸው ይታወቃሉ፡” ብሏል። እያችሁ፡ ፍሬ! እነዚህ ነገሮች በውስጣችሁ ካልያዛችሁ ፍሬ ማፍራት አትችሉም። እናም እግዚአብሔርን አለመፍራት እና—እና የመሳሰሉት፡ ይህ ሁሉ ዓለማዊነት ቦታ ሲይዝ፡ ያን ጊዜ አለማመን ሁሉ ይጠፋል፡ ያኔ የአለም ነገሮች ሁሉ ያልፋሉ፡ ያኔ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ካልሆነ በቀር ምንም የለም። እና ከዚያም ኤፌሶን 4፡30፡ “ለቤዛችሁም ቀን የታተማችሁበትን፡ የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ” ይላል። አሁን ለእግዚአብሔር መንግሥት ታትማቿል! አሁን፡ ያንን አትርሱ። ያንን አሁን አትርሱ፡ ከሁሉ በፊት **እነዚህ** ነገሮች ይጠይቃል። ከዚያም ከአካሉ ጋር የሚያትመን፡ ማኅተሙ መንፈስ ቅዱስ ነው። መልካም።

3 አሁን አንድ—አንድ ጥያቄ በቺካጎ ለምትኖረው ለእህት ሊትል፡ ተጠይቀናል፡ እህት ሊትል፡ ባለቤቷ የመኪና አደጋ አጋጥሞታል እና በሞት አፋፍ ላይ ነው። እና ኢዲት ራይት፡ እዚህ ለረጅም ጊዜ የምናውቃት ታናሽ እህታችን፡ ዛሬ ማታ፡ በቤቷ ውስጥ፡ በጣም በጣም በመጥፎ ሁነታ ላይ ነች፡ እናም ሁላችንም ለዚህ ጥያቄ አብረን እንድንፀልይ ይህንን ለቤተክርስቲያን ማስታወቅ ፈልገዋል። እና አሁን ለአፍታ ያህል አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

4 ውድ፡ የሰማይ አባታችን፡ በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ (በእምነት) እየተሰበሰብን ነው፡ እናም ለእነዚህ ጥያቄዎች መለኮታዊ ምህረትን እንጠይቃለን። ወንድም ሊቲል፡ በመኪና አደጋ፡ ለሞት ተቃርቧል። እግዚአብሔር ሆይ፡ እርዳው። አቤቱ አምላካችን፡ መንፈስ ቅዱስ በአልጋው ዙርያ ሆኖ ወደ እኛ ይመልሰው። ትንሿ ኢዲት ራይት ደግሞ እዚያ አለች፡ መንፈስ ቅዱስ ዛሬ ማታ በአልጋዋ አጠገብ ሆኖ ጤናዋን እንደገና እንዲመልስላት፡ እግዚአብሔርን፡ እጸልያለሁ። አድርገው፡ አባት ሆይ። እነዚህን ነገሮች ቃል ገብተሃል፡ እናም እናምናቸዋለን። እና ዛሬ ጠዋት እያሰብን እንደነበረው፡ ርቀት ማለት ለአንተ

ምንም አይደለም፡ አንተ እንደ ሌላው የዓለም ክፍል ታላቅ ነህ፡ ምክንያቱም አንተ በሁሉም ቦታ የምትገኝ፡ ሁሉን ቻይ፡ እና ማለቂያ የለለህ ነህ። እና አባት ሆይ፡ እኛ እንጸልያለን: እነዚህን ጥያቄዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንድትሰጠን። አመን።

5 ዛሬ ማታ በድጋሚ እዚህ በመገኘቴ በጣም ደስተኛ ነኝ፡ ወደ... እና እንደሚሞቅ አውቃለሁ። እነዚህ ሶስት ተከታታይ ስብሰባዎች ናቸው፡ እና... አንዳንዶቻችሁ በአሁን እና በጥዋት መካከል ለመንዳት እስከ አምስት መቶ ማይል እንደሚጠብቃችሁ አውቃለሁ። እና እኔ ከነገ ጀምሮ፡ ከዛ በኋላ ለመንዳት አስራ አራት መቶ አገኛችያለው። ስለዚህ፡ ስለዚህ እኔ—እኔ ለሁላችሁም ታላቅ ጊዜ እንደነበረ አምናለሁ። እና ለእኔ ከእናንቴ ጋር ለመጎብኘት ጥሩ ጊዜ ነበር። እኛ የጠየቅነው አንድ ነገር ብቻ ነው፡ ብዙዎች እንዳይገቡ መከልከል ነበረባቸው ምክንያቱም ቦታ ስለሌለ፡ መተላለፊያዎቹን ከልክ በላይ ማጨናነቅ አንችልም፡ የእሳት አደጋ ክፍል ለዚያ አይቆምም። ስለዚህ አሁን ትንሽ ተለቅ ያለ ቤተክርስትያን ለማግኘት እየሞከርን ነው፡ ይህም ስንገባ፡ እና ለሰዎች መቀመጫ እንዲኖረን ነው።

6 እና አሁን፡ በማንኛውም ጊዜ፡ ወደ ቤተክርስትያናችን ሁል ጊዜ መምጣት ትችላላችሁ፡ እኛ ሀይማኖት የለንም ነገር ግን ክርስቶስ አለን፡ ህግ የለንም ግን ፍቅር አለን፡ መጽሐፍ የለንም ግን መጽሐፍ ቅዱስ አለን። እና ስለዚህ... እና የእኛ ፓስተር እዚህ ወንድም ኦርማን ኔቪል ነው። እናም እዚህ—እዚህ መጥታችሁ ህሊናችሁ እንደ ፈቀደ እግዚአብሔርን የምታመልኩበት፡ ብዙ ሰዎች አንድ ላይ እንደ ቤተ እምነቶች መገናኛ ዲንኳን ሆነው የሚሰበሰቡበት ጉባኤ አለን። እናንተን በማግኘታችን ሁሌም ደስተኞች ነን። እና ስለዚህ በሚትችሉበት ጊዜ ኑ፡ እኛ እናንተን ለመቀበል ሁል ጊዜ ደስተኞች ነን።

7 እና አሁን በሚቀጥለው ጊዜ፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ፡ ከእናንተ ጋር የምሆነው፡ ቤተክርስቲያኑ ካለቀ በኋላ ይሆናል። እናም **ከቤተክርስቲያን ዘመናት** በኋላ፡ ያንን ለማስተማር ወደ ሰባቱ የመጨረሻዎቹ **ማኅተሞች**፡ እና በራዕይ መጽሐፍ ውስጥ ወደ ሰባቱ የመጨረሻዎቹ **ማኅተሞች**፡ መሄድ እፈልጋለው።

8 እና አሁን ብዙ ጊዜ በእነዚህ ራእዮች በሚያስፈልጉባቸው ስብሰባዎች፡ ብዙ የታመሙ፡ እና የተጨነቁ ይመጣሉ፡ እና ለልዩ ቃለ መጠይቅ ይመጣሉ። እዛ ወስጥ ከገባሁ፡ እኔ—እኔ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ማግኘት አልቻልኩም፡ እና፡ አይሆንም፡ ከዚያ በኋላ መናገር ይከብደኛል። እናም በእኛ የፈውስ ዘመቻዎች ውስጥ አቶ ባክስተር ወይም ለላ ሰው ብዙውን ጊዜ እንደሚሰብክ ሁሉም ሰው ያውቃል፡ እና እኔ ለታመሙ ለመጸለይ እወጣለሁ፡ ምክንያቱም እሱ ትንሽ ከባድ ነው። እና ከጥቂት ጊዜያት በፊት ለአንዳንድ ሰዎች እየጸለይኩ ነበር፡ ሰለሱ ዶክተሮች የሆነ ነገር ያሉት ጨቅላ ልጅ አገኘሁት... ጀርባው ላይ የሆነ ነገር፡ በሆነ መንገድ የተወለደ ነው። ወደ ውጭ ሰወጣ፡ እዚያ በጉባኤው ውስጥ ተቀምጦ አየሁት። ያ ልጅ በጭራሽ እንደዚህ አይነት አካል ጉዳተኛ መሆን የለበትም፡ ደህና ሊሆን ነው። በእርግጥ፡ እንደዛ ነው፡ እያችሁ። ያ ነው፡ ያንን አውቃለሁ። እያችሁ፡ እኔ ለዛ አዎንታዊ ነኝ። ስለዚህ እምነት እንዲኖረን እና በእግዚአብሔር ማመን እንፈልጋለን።

9 እያንዳንዳችሁ፡ ሁሉም አገልጋዮች፡ እና ሌሎችም እና ብዙዎቻችሁ ለእኔ እንግዶች ናችሁ። ካልተሳሳትኩ፡ ይህ ወንድም ክሬስ ነው። ልክ ነው? ወንድም ክሬስ፡ እኔ—እኔ በዛ ቆራጥነት ላይ ስላልደረስኩ ይቅርታ ልጠይቅህ፡ ይገባኛል። ምናልባት በሚቀጥለው ሳምንት መጨረሻ ባለን ስብሰባ እደርስ ይሆናል፡ ብቻ ደህና ሁን። ትክክል ነው? እዛ ላይ ብሉሚንግተን። ደህና ነህ? መልካም። ከእነዚህ ወንድሞች መካከል አንዳንዶቹ አገልጋዮች ናቸው፡ ብዬ አስባለሁ። አገልጋይ ነህ? አዎን፡ ጌታዬ። ጌታ ይባርክህ። እና ህንፃው ውስጥ ስንት አገልጋዮች አሉችሁ፡ እስቲ እጃችሁን እንይ። መልካም፡ ያ ጥሩ ነው። እናንተን እዚህ በማግኘታችን ደስተኞች ነን፡ በጣም ደስ ብሎናል። እግዚአብሔር ሁሌም ይባርካችሁ!

10 አሁን፡ በጊዜ እንድንወጣ ከዛሬ ምሽት ጀምሮ፡ አንዳንዶቹ ወደ ጆርጂያ፡ ቴነሲ፡ ኒውዮርክ፡ በሁሉም ቦታ፡ ከምሽቱ ጀምሮ፡ ይሄዳሉ። አሁን፡ በመንገዱ ላይ በጥንቃቄ አሽከርክሩ። እንቅልፍ ከያዛችሁ፡ ወደ መኪና ማቆሚያ መሄድ አይጠበቅባችሁም፡ ከመንገዱ ዳር ውጡ እና እስኪበቃችሁ ተኙ… እኔ እንደዛ ነው የማደርገው። አያችሁ፡ ዝም ብላችሁ ከመንገዱ ወጣ ብላችሁ ተኙ። በጭራሽ፡ እንቅልፍ ይዞአችሁ በጭራሽ አትንዱ። መጥፎ ነገር ነው። እና፡ አስታውሱ፡ ራሳችሁን አይደለም፡ ማየት ያለባችሁ አጠገባችሁ ያለውን ጓደኞችሁን ነው። አያችሁ? እናንተ የት እንደምትሄዱ ታውቃላችሁ፡ እሱ ወዴት እንደሚሄድ አታውቁም፡ ስለዚህ—ስለዚህ ያንን ሰው መጠበቅ አለባችሁ። ስለዚህ፡ እሱን ለመከታተል፡ ሁል ጊዜ ንቁ መሆናችሁን እርግጠኛ ሁኑ።

11 አሁን፡ ዛሬ ማታ በቅዱስ ዮሐንስ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘውን የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል ለማንበብ እፈልጋለሁ። አሁን፡ እነዚህ የምናነብባቸው እና የምንጠቅሳቸው ትንንሽ ቅዱሳት መጻሕፍት፡ ለመናገር የምንፈልገውን መሠረታዊ ነገር እንዲሰጡን ነው። እና ሁሌም፡ እንደማስታውሰው፡ በጭራሽ አንድ ጊዜም ቢሆን፡ ወደ መስዊያው ስመጣ፡ አንድ ነገር ማለት ስላለብኝ ብቻ ብዬ አላውቅም። ህዝቡን የሚረዳ አንድ ነገር እንዳለኝ እስኪሰማኝ ድረስ ሁል ጊዜ ለመጠበቅ፡ ለመመልከት፡ ለማጥናት፡ ለመጸለይ፡ እሞክራለሁ። እኔ መርዳት ካልቻልኩ፡ እዚህ መቆም አያስፈልገኝም፡ አያችሁ። ለማገዝ መሞከር፡ ነው! እና አሁን ዛሬ ማታ፡ በእርግጥ፡ አብዛኛው የህዝባችን ክፍል በጠዋት ተነስቷል፡ እና ብዙዎቹ፡ ወደ ቤት መሄድ ነበረባቸው። ግን፡ ዛሬ ማታ፡ ብትቆዩ ኑሮ ይጠቅመናል ብዬ ተስፋ በማደርገው ነገር ላይ ለአርባ-አምስት-ደቂቃ ያህል ለመነጋገር እንደምንሞክር ነግሪያችሁ ነበር። ይህንንም አሁን በቅዱስ ዮሐንስ ምዕራፍ 16፡ ላይ መሰረት እናደርጋለን፡ እና በ—በ16ኛው ምዕራፍ 7ኛ ቁጥር፡ እንጀምርና እስከ—እስከ 15ኛው ቁጥር ድረስ እናነባለን።

**እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፡ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል፡ እኔ ባልሄድ፡ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፡ እኔ ብሄድ፡ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ።**

**እርሱም መጥቶ፡ ስለ ኃጢአት፡ ስለ ጽድቅም፡ ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፡**

**ስለ ኃጢአት፡ በእኔ ስለማያምኑ ነው፡**

**ስለ ጽድቅም፡ ወደ አብ ስለምሄድ፡ ከዚህም በኋላ ስለማታዩኝ ነው፡**

**ስለ ፍርድም፡ የዚህ ዓለም ገዥ ስለ ተፈረደበት ነው።**

**የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፡ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም።**

**እርሱ፡ የእውነት መንፈስ፡ በመጣ ጊዜ፡ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፡ የሚሰማውን ሁሉ፡ ይናገራል እንጂ፡ ከራሱ አይነግርምና፡ የሚመጣውንም ይነግራችኋል።**

**እርሱ፡ ያከብረኛል፡ ለእኔ ካለኝ ወስዶ፡** ይነግራችኋልና።

**ለአብ ያለው ሁሉ** የ—**የእኔ ነው፡ ስለዚህ ለእኔ፡ ካለኝ ወስዶ፡** ይነግራችኋል **እልሁ።**

12 አሁን በዚህ 13 ኛ ቁጥር። "ነገር ግን የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፡ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል። የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፡ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል።" እውነት ምንድን ነው? ቃሉ። "እርሱ ይናገራልና፡ ከራሱ አይናገርም፣ የሚሰማውን፡ ግን ይናገራል። የሚሰማውን፡ ይናገራል።" በሌላ አነጋገር፡ ነገሩን የሚገልጥ እርሱ ይሆናል፡ አያችሁ። በዕብራውያን ምዕራፍ 4 ላይ ደግሞ፡ መጽሐፍ ቅዱስ "የእግዚአብሔር ቃል የተሳለ፡ ሁለትም-አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የሚበረታ፡ የ—የልብንም ስሜትና አሳብ፡ ይመረምራል" ይላል። አያችሁ፡ "የሚሰማውን፡ ይናገራል፡ እና የሚመጣውንም ያሳያችኋል።" አያችሁ? ምንድነው ያንን የሚያደርገው? በጌታ በኢየሱስ ስም የሚመጣው መንፈስ ቅዱስ።

13 እና ትኩረታችሁን "መሪ"፡ በሚለው ቃል ላይ በማድረግ እነዚህን የሚቀጥሉትን ጥቂት ደቂቃዎችን መዉሰድ እፈልጋለሁ **መሪው።** ታውቃላችሁ፡ ጫካ ውስጥ ጥሩ ልምድ አግኝቻለሁ። መሪ፡ ማለት የሆኔ ሰው ዙሪያችሁን ሊያሳያችሁ የሚችል ሰው። ወዴት እንደሚትሄዱ ካላወቃችሁ መሪ ሊኖራችሁ ይገባል። እና ከአደን ጋር በመተዋወቄ፡ እና በዙሪያው ካለው አለም ጋር በመተዋወቄ፡ የሚመሩትን አሰጎብኚዎችን የማግኘት—እድል አግኝቻለሁ። እና እኔ በኮሎራዶ ውስጥ፡ እኔ ራሴ፡ መሪ ነኝ፡ ምክንያቱም እርባታ፡ ወዘተ፡ አገሩን ስለማውቅ፡ በኮሎራዶ ውስጥ ማስጎብኘት እችላለሁ።

14 አሁን፡ መሪ መንገዱን ማወቅ አለበት። የት እንደሚሄድ እና ምን እንደሚሰራ፡ እና በመንገድ ላይ እናንተን እንዴት እንደሚንከባከቡ ማወቅ አለበት። አያችሁ? ጠፍታችሁ እንዳትገኙ ማየት አለበት። መሪ የተመረጠ ሰው ነው። ይህ ሰው መሪ ከሆኔ፡ ብድኑ ይመርጠዋል። አሁንም፡ ወደ ምድረ በዳ ጉዞ ላይ ሰትሄዱ፡ ምናልባት፡ መሄድ ያልለመዳችሁበት፡ ያለ ምንም መሪ መሄድ ጥሩ ነገር አይደለም። እውነቱን ለመናገር፡ አንዳንድ ቦታዎች ያለ መሪ መሄድ አትችሉም፡ ለምሳሌ፡ ካናዳ። መሪው የ—የእናንተን ፈቃድ ለጨዋታ ጠባቂው መፈረም አለበት። እሱ ራሱን ማሰገባት አለበት፡ እና እሱ ለናንተ ተጠያቂ ነው። በእናንተ ላይ የሆነ ነገር ቢከሰት፡ የእርሱ ኃላፊነት ነው። እርሱ እናንተን መንከባከብ አለበት። እንዳልጠፋችሁ ማየት መቻል አለበት። የመመለሻ መንጌዳችሁን ወደማታውቁበት ቦታ እንደማይልካችሁ እርግጠኛ መሆን አለበት። እና ከጠፋባችሁ፡ ደግሞ አገሩን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ በማንኛውም

ጊዜ ሊወስዳችሁ ይችላል። እነዚህን ሁሉ ነገሮች ማወቅ አለበት ወይም አለዚያ መሪ ሊሆን አይችልም፡ መሪ ለመሆን ፈቃድ ሊሰጡው አይችልም።

15 ለእነዚህ ነገሮች፡ አንዳንድ ጊዜ ቀጠሮ መያዝ አለባችሁ፡ ቀድማችሁ ደውላችሁ እና ዝግጅት ማድረግ፡ ቦታ ማስያዝ አለባችሁ። እና የእናንተ... አንዳንድ ጊዜ ቦታ ተሞልቶ ከሆነ እና ሊወስዳችሁ ካልቻለ፡ ከ—ከምድራዊው መሪ ጋር፡ ለተወሰነ ጊዜ ቀጠሮ ማራዘም አለባችሁ። ያንን ከእግዚአብሔር መሪ ጋር በፍጹም ማድረግ የለባችሁም፡ እሱ ሁል ጊዜ ዝግጁ ነው፡ ሁል ጊዜም ዝግጁ ነው።

16 አሁን፡ እነዚህን ዝግጅቶች ካላደረጋችሁ፡ እና ከዚህ ቀደም ያልነበረባችሁትን ምድረ በዳ ውስጥ ለመጓዝ እያሰባችሁ ከሆነ፡ ጠፍታችሁ ልትገኙ፡ እና ልትጠፉ ትችላላችሁ። ከበረሃ ለመውጣት አንድ በመቶ ያህል እድል ታገኛላችሁ፡ ማለትም፡ በጣም ጥቅጥቅ ያለ ካልሆነ፡ ብቻችሁን ለመውጣት አንድ በመቶ ያህል ዕድል ሊኖራችሁ ይችላል። ነገር ግን በጣም መጥፎ ምድረ በዳ ከሆነ፡ ወደ ኋላ ለመመለስ፡ እድል አታገኙም። ይህን የሚታደርጉበት ምንም ዕድል የለም፡ ምክንያቱም እራሳችሁን በሞት መንገድ ላይ ታገኛላችሁ፡ እና ከዚያም—ጨርሳችኋል፡ አብቅታችኋል። አሁን፡ እና አገሩን የሚያውቅ እና እንዴት እንደሚትመለሱ የሚያውቅ መሪ ከሌላችሁ ትጠፋላችሁ።

17 ብዙዎቻችሁ ባለፈው አመት በቱክሰን፡ አሪዞና፡ ስለ እነዚያ ታዳጊ ስካውቶች ያነበባችሁትን ጽሁፍ ታስታውሳላችህ። ሆኖም፡ ራሳቸውን እንዴት መንከባከብ እንዳለባቸው እንዲያውቁ የሰለጠኑ፡ ስካውቶች ነበሩ። እና እነሱ የህጻናት ስካውቶች ብቻ ሳይሆኑ፡ አዋቂ ስካውቶች ነበሩ። እናም ወደ ተራራዎች ጉዞ አደረጉ፡ እና የበረዶ አውሎ ንፋስ መጣ፡ ተፈጥሮ ሁነታውን ቀየረ። ሁሉም መንገድ ሰተው እና ራሳቼውን ጠፍተው ባዩ ጊዜ፡ ምክንያቱም... ከተለመደው፡ የተለየ ነገር ሲመጣ፡ እንዴት መውጣት እንዳለባቸው አላውቁም ነበር። አያችሁ? እናም በተራራው ላይ ሰንት ታዳጊዎች እንደጠፉ አላስታውሰም፡ ሄሊኮፕተሮች፡ እና ሚሊሻዎች፡ እና ብሄራዊ ጥበቃዎች፡ እና የበጎ ፈቃደኞች እርዳታ፡ እና ሁሉም ነገር ነበራቸው። ይሁን እንጂ ጠፍተዋል፡ የት እንዳሉ ማንም አያውቅም። እና በራሳቸውን መውጣት አልቻሉም። ሁሉም በበረዶው ውስጥ ጠፍተዋል ምክንያቱም ወደ ምስራቅ ይሁን፡ ወደ ሰሜን፡ ወደ ምዕራብ ወይም ወደ ደቡብ፡ ወደ ላይ ወይም ወደ ታች፡ እንደሚሄዱ ወይም እንዴት እንደነበረ፡ ስለማያውቁ ሁሉም ነገር ተመሳሳይ መሰላቸው።

18 አሁን፡ የአየር ሁኔታው ምንም ቢሆን፡ መሪው የት እንዳለ ያውቃል። እሱ—እሱ ያንን ለመፈጸም ታጥቋል። የሚያደርገውን ያውቃል። ስለ ሁሉንም ነገር ልምድ አለው፡ የሁሉንም ነገር ገጽታ ያውቃል፡ ስለዚህም በጨለማ ውስጥ ሆኖ እንኳን የሚታይ ነገር ሊሰማው ይችላል።

19 ለምሳሌ፡ የመሪ አንድ የቆዬ ዘዴ ይኸውና። ታውቃላችሁ፡ ኮከቦችን ማየት ከቻላችሁ፡ ከዋክብትን የምትመለከቱ ከሆነ ማንኛውም ሰው የትኛውን መንገድ እንደምትሄዱ ሊነግራችሁ ይችላል። እና ሁልጊዜ አንድ እውነተኛ ኮከብ ማየት ትፈልጋላችሁ። አንድ ብቸኛው እውነተኛ ኮከብ አለ፡ እና ይህም የሰሜኑ ኮከብ ነው። ኣያችሁ፡ አንድ ብቻ፡ እሱ በተመሳሳይ ቦታ ቆሟል። ይህም የሚወክለው ትናንትና፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው የሆነውን፡ ክርስቶስን ነው።

ሌሎች ሊለዋወጡ ይችላሉ፡ እርሱ ግን ያው ነው። አብያተ ክርስቲያናት **በዚህ** መንገድ ሊያወጧችሁ ይችላሉ፡ ወይም አንዳንዶች **በዛ** መንገድ ሊያወጧችሁ ይችላሉ፡ እሱ ግን አይደለም፡ እሱ ሁል ጊዜም የማይቀየር ነው።

20 ደህና፡ አሁን፡ ይህን የሰሜን ኮከብ ማየት ካልቻላችሁ፡ እና ደመናማ ከሆነ፡ ከዚያም ካስተዋላችሁ፡ ቀን ከሆነ እና ከጠፋባችሁ፡ ዛፎችን የምትመለከቱ ከሆነ። ዛፍ ሁል ጊዜ፡ የድንጋይ ሽበት የሚበዛበት በዛፉ በስተሰሜን በኩል ነው፡ ምክንያቱም የዛፉ ደቡባዊ ክፍል ከሰሜን ይልቅ ፀሀይን ያገኛል። ግን ጨለማ ከሆነ እና የድንጋይ ሽበቱን ማየት ካልቻላችሁስ? ዓይናችሁን ጨፍናችሁ እና ምንም ለማሰብ አለመሞከር፡ ዓይናችሁን ጨፍኑ እና የተንቆጠቆጠ-ዛፍ ያዙ፡ ጣቶቻችሁ እስኪዳብሱት ድረስ እጆቻችሁን በዛፉ ዙሪያ እንዲህ አድርጉ፡ እና ከዚያ በዛፉ ዙሪያ በዝግታ መንቀሳቀስ ጀምሩ። እና ቅርፊቱ የእውነት ወፍራም የሆነ፡ የተሰበረ ቦታ ስታገኙ፡ ያ የሰሜን በኩል (ነፋስ) ነው፡ እና ወደ ሰሜን ወይም ደቡብ፡ ወደ የትኛው መንገድ እንደሚትሄዱ መናገር ትችላላችሁ። እና በዚያ መንገድ፡ ኦህ፡ ብዙ ነገሮች አሉ፡ ግን እነዛን ነገሮች እንዴት ማድረግ እንዳለብን ለማወቅ መመሪያዎችን ይፈልጋል። አንድ ተራ ሰው ወደዚያ ይነሳና እንዲህ ይላል፡ “በዚህ ምንም ልዩነት አልተሰማኝም።” አያችሁ? አያችሁ፡ ለዚያ መሪነት መሰልጠን አለባችሁ።

21 እና እነዚያ ታዳጊዎች፡ ያለ ምንም ጥርጥር የደረሱ ሰካውቶች ነበሩ፡ ምናልባት ከረባት ማሰር ይችሉ ይሆናል፡ ምናልባት ድንጋይ ተጠቅመው እሳት መፍጠር፡ እና የመሳሰሉትን ነገር ማድረግ ይችሉ ይሆናል። ግን መውጫ መንገዳችሁን ማወቅ፡ ያ ትክክለኛ ነገር ነው! እነርሱ፡ መውጫቸውን አያውቁም ነበር፡ ስለዚህ ሁሉም ጠፉ ምክንያቱም ከእነርሱ ጋር የሚሄድ የሚመራቸውን ሰው አልወሰዱም ነበር።

22 ከሁለት አመት በፊት፡ በኮሎራዶ፡ አንድ ያልታሰበ አባት፡ ኦህ፡ ወደ ተራራ እየወጣ ነበር፡ የሰድስት ወይም የሰባት ዓመት ልጅ፡ ትንሽ ልጅ ይዞ ነበር። አጋዘን ወደ ማደን ለመጀመሪያ ጊዜ እየወሰደው ነበር። ወደ ተራራው ከፍ ብለው ወጡ፡ ሕፃኑም አባቱን፡ “እየደከመኝ ነው” አለው።

23 “ጀርባዬ ላይ ውጣ። ገና ከፍ ብለን አልወጣንም፡ አጋዘኖቹ ያሉት ከፍታው ላይ ነው።” ሰውዬውን እስከሆነ ድረስ ቀጠለ… የከተማ ሰው ስለነበር፡ አያውቅም ነበርና። እንዴት ማደን እንዳለበት ወይም የት መሄድ እንዳለበት ምንም አያውቅም ነበር። ስለ ምድረ በዳ የሚያውቅ ማንኛውም ሰው አጋዘን ተራሮች ላይ እንደማይኖሩ ያውቃል። አጋዘኖች ወደ ከፍታ አይሄዱም። ፍየሎች ከፍታ ላይ ይወጣሉ፡ አጋዘኖች ግን አይወጡም። እነሱ መመገብ በሚችሉበት ቦታ ዝቅ ብለው፡ የሚበላ ነገር ወዳለበት ቦታ መድረስ አለባቸው። ስለዚህም፡ ግን፡ ይህ ሰው ያሰበው፡ “ወደ ላይ በድንጋዮች መካከል ብወጣ፡ ትልቅ ወንድ አጋዘን አገኛ ይሆናል” ብሎ አስቦ ነበር። አንዳንዶች ቆመው—በድንጋይ ላይ ቆመው የተነሱትን ምስል አይቶ ነበረና፡ እርሱን የሚያገኝበት ቦታ እዚያ እንደሆነ አሰበ። መጽሔቶችን ለሚያሰነብቡት ትኩረት አትስጡ ትቃዣላችሁ፡ ማይ፡ ኦህ፡ ማይ፡ በጣም ይገርማል! መደረግ ያለበት አንድ ነገር ቢኖር፡ ያ ነው፡ የት እንዳላችሁ የምታውቁት፡ እስጎብኚ ከወሰዳችሁ ነው።

24 እና ያ አባት፡ በአንዴ የዝናብ ዶፍ መጣበት፡ ከዝናቦችም መካከል ፈጠን

ያለ ዝናብ መጣ። እናም ሰውዬው ያደነው በጣም ዘግይቶ ነው፡ እስኪጨልም ድረስ እና ወደ ኋላ የሚመለስበትን መንገድ ማግኘት አልቻለም። እናም ከዛ... ከተራሮች ጫፍ ላይ ንፋስ መጣ፡ እና እሱ ራሱ በፍጥነት ይጓዛል፡ እና ያ...

25 ከተያዛችሁ፡ እንዴት እንደሚትተርፉ ማወቅ አለባችሁ። ሌላ መሆን ያለበት ነገር፡ እንዴት እንደሚትተርፉ እወቁ! እኔ በህይወት ለመቆየት ዛፎችን ወደ ላይ ወጥቼ ወደ ታች ተንሸራትቻለሁ፡ ዛፎችን እወጣለሁ ወደ ታች እንሸራተታለሁ፡ ወደላይ እና ወደ ታች፡ እንደዛ አድርጌአለሁ። በረዶ በእያንዳንዱ ጎን አራት ጫማ በሚሆንበት ጊዜ ደርሻለሁ፡ ጉቶ ፈልጬ ደረደርኩት። እና በጣም ስለራበኝ ልቋቋመው አልቻልኩም! እና እነዚህን ያረጁ ጉቶዎችን ፈልጬ፡ ለኮስኳቸው እና እንዲሞቅ እና በረዶው እንዲቀልጥ አደረግኩ። ከዚያም ከጠዋቱ አንድ ሰዓት፡ ወይም ሁለት ሰዓት፡ በሕይወት ለመቆየት፡ ጉቶዎቹን አንስቼ፡ በዚያ ሞቃታማ መሬት ላይ ተኛሁ። እና እነዚህን ነገሮች እንዴት ማድረግ እንዳለባችሁ ማወቅ አለባችሁ።

26 እናም ይህ ሰው የሚያደርገውን አያውቅም ነበር፡ ከእርሱ ጋር የሚመራው ማንም አልነበረውም። እናም የራሱን ታናሽ ልጅ ቀዝቅዞ እስኪሞት ድረስ በእቅፉ ላይ አድርጎት ነበር። ያልታሰበ ነገር! እሱ ገና ከራሱ ጋር አሰጎብኚ ቢወስድ ኖሮ፡ እያችሁ፡ ጊዜው ምንም ይሁን ምን ወዲያው ከተራራው ሊመልሰው ይችል ነበር። ግን እስኪጨልም ድረስ ጠበቀ፡ ከዚያ መንገዱን ማየት አልቻለም ነበር።

27 ዛሬ በክርስቲያኖች ላይ ያለው ችግርም ይህ ነው። ጨለማው እስከሚሰፍር ድረስ ይጠብቃሉ፡ ከዚያ ያለ መሪ እንደወጣችሁ ታውቃላችሁ። መሪ!

28 ለምን፡ የጠፋ ሰው አይታችሁ ታውቃላችሁ? የጠፋውን ሰው በማምጣት ልምድ ያለው ሰው አለን? እስካሁን ካያችሁት ነገር በጣም አሳዛኝ ነገር ነው። ሰው ሲጠፋ፡ ጫካ ይሄዳል። የሚያደርገውን ነገር አያውቅም። እዚያ አንድ ወንድ ልጅ፡ አግኝተነው፡ እና በጫካ ውስጥ ጠፍቶ ነበር፡ እናም እሱ ያሰበው... የእርባታ ሰራ ይሰራ ነበር፡ ግን በተሳሳተ ክልል ውስጥ ገባና እና ጠፋ፡ በተቃራኒ መንገድ ሄደ። እና ከሶስት ቀን በኋላ ሲያገኙት፡ ልክ እንደ ጫካ ሰው እየሮጠ፡ ድምፁን ከፍ አድርጎ ሲጮኽ ነበር። ከንፈሮቹ ሁሉ ተበልተዋል፡ እና ሸጉጡን ጣለው እና ምን ማድረግ እንዳለበት አያውቅም ነበር። እና የገዛ ወንድሙ፡ ሊ... ሊዩዙትና ሊያሲሩት በነበረባቸው ግዜ። የገዛ ወንድሙ ወደ እርሱ ሲመጣ፡ እንደ እንስሳ ሲታገለው ነበር፡ ሊነክሰው ሞከረ፡ የት እንዳለ ራሱን አያውቅም ነበር። ለምን? እሱ ጠፍቶ ነበር። እና ሰው ሲጠፋ፡ ግራ በመጋባት ውስጥ ይገባል። እና እሱ ራሱን በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዳለ አያውቅም ነበር፡ ምክንያቱም መጥፋቱ ትኩሳት ይለቅበታል፡ እና የት እንዳለ እና እንዴት እንደሚሆን አያውቅም።

29 ሰውም ከእግዚአብሔር ሲጠፋ እንዲሁ ነው! ከዚህ በፊት የማያደርጋቸውን ነገሮች ያደርጋል። የሚደርገው ነገር—ከሰው ልጅ አስተሳሰብ በላይ ይሆናል። ከእግዚአብሔር የጠፋ ሰው፡ ከእግዚአብሔር የጠፋች ቤተ ክርስቲያን፡ ከእግዚአብሔር የራቀች፡ ከእግዚአብሔር የመጽሐፍ ቅዱስ መርሆች የራቀች ቤተ ክርስቲያን፡ አንዳንድ ጊዜ በሕያው በእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይገኛሉ ብላችሁ የማትጠብቁትን ነገር ያደርጋሉ። ገንዘባቸውን በቡንኮ ጨዋታዎች፡ ሎተሪ በመጫወት፡ በቁማር፡ በሚችሉት ማንኛውም ነገር ያገኛሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ከፋይ ከሆነ

ሰውዬውን ጀርባው ላይ አሸት አሸት እያደረጉ፡ ማንኛውም ነገር እንዲሆን ይፈቅዳሉ፡ ማንኛውም ነገር ያስተምራሉ፡ እና እንደዚያ ያሉ ነገሮችን፡ ያደርጋሉ። ያ እውነት ነው። አራት ወይም አምስት ጊዜ ያገቡ ሰዎች ዲያቆናት በቦርድ ይሾማሉ፡ በዚያም እንዲያልፍላቸው፡ ኑሮን ለማሟላት ነው። ታሟሉት የሚገባችሁ አንድ ነገር ብቻ ነው፡ ይህም፡ለእግዚአብሔር ያላችሁ ግዴታ ነው። ቁሙ እና እውነቱን ተናገሩ! የጠፋ፡ የጠፋ ሰው ግራ በተጋባ ሁኔታ ውስጥ ነው፡ ያብዳል።

30 መሪው እንዴት እንደሚሄድ እና ምን ማድረግ እንዳለበት፡ ግንዛቤ አለው። እግዚአብሔር... እግዚአብሔርም ሁል ጊዜ ለህዝቡ መሪ ይልኳል። እግዚአብሔር ፈጽሞ ተሳስቶ አያውቅም። እሱ መሪ ይልካል፡ እናንተ ግን መሪውን መቀበል አለባችሁ። አያችሁ? ማመን አለባችሁ። እሱ የሚናገረውን መንገድ መሄድ አለባችሁ። ምድረ በዳ ውስጥ ከገባችሁ፡ እና መሪያችሁ "**በዚህ** መንገድ እንሄዳለን" ሲላችሁ፡ እናንተ ግን **በዚያ** መንገድ የምትሄዱ ይመስላችኋል፡ ያኔ በዚያው ትጠፋላችሁ። ከዚያም እራሳችሁን... እግዚአብሔር የሚመራን መሪ ይልክልናል፡ መሪውን መከተል አለብን። ምንም ብናስብ፡ ምክንያታዊ ቢመስለን እና ምንም የማይሆን ቢመስልም፡ እኛ ያንን የምንከፋፍል አይደለንም፡ መሪው አንድ ብቻ ነው።

31 እግዚአብሔር፡ በብሉይ ኪዳን፡ ነቢያትን ላከ። የጌታ ቃል ስለሚመጣላቸው፡ መሪዎች ነበሩ። መሪዎች ነበሩ። ትላንት ምሽት እንዳየነው፡ ኢሳያስና ያዚያ ህዝቡን አስተምረዋል። እነርሱ የተማሩ ነበሩ፡ ሕዝቡንም አስተምረው መርተዋል። እና አሁን እግዚአብሔር ሁል ጊዜ መሪዎችን ይልካል፡ በሁሉም ዘመናት፡ ሁል ጊዜ መሪ አልባ ሆኖ አያውቅም። እግዚአብሔር ሁልጊዜም በሁሉም ዘመናት በዚህ ምድር ላይ፡ እርሱን የሚወክል አካል ነበረው።

32 አሁን፡ አንዳንድ ጊዜ ከመመሪያው ይወጣሉ፡ "የስህተት መንገድ፡" ብለን እንጠራዋለን። ኢየሱስ እዚህ ምድር ላይ ሳለ፡ ለፈሪሳውያንን፡ "እናንተ ዕውሮች መሪዎች" እንዳላቸው አታስታውሱም? ዕውሮች መሪዎች፡ ለመንፈሳዊ ነገሮች ዕውሮች። አያችሁ? አሁን፡ መሪ ሊሆኑ ይገባ ነበር፡ ሕዝቡን የሚመሩ፡ ሕዝቡን ወደ ደህንነት የሚመሩ መሆን ነበረባቼው። ኢየሱስ ግን "ዕውሮች ናችሁ!" አላቸው፡ እርሱም፡ "ተዉአቸው፡ ዕውር ዕውርን ቢመራ፡ ሁለቱም በገደል ውስጥ አይወድቁምን?" አለ ዕውሮች መሪዎች! ኦህ፡ አለም እንዴት በነዛ እውራን መሪዎች፡ ተበከለች። እርሱ በራስ መረዳት እንድትተማመኑ አይፈልግም። እግዚአብሔር በማስተዋልህ ወይም በሃሳብህ፡ ወይም በማናቸውም ሰው-ሰራሽ ሀሳቦች እንድትመካ አይፈልግም።

33 እግዚአብሔር መሪን ይልካል፡ እና እግዚአብሔር ያ መሪ እርሱ የሾመው መሪ መሆኑን እንድታስታውሱ ይፈልጋል። እሱንም ልናስታውሰው ይገባል። እዚህ ላይ፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ "እንዲሁ አልተዋችሁም፡ ነገር ግን አብን እጸልያለሁ ሌላ አጽናኝ ይልክላችዋል።" እናም ይህ አፅናኝ፡ በሚመጣበት ጊዜ፡ ወደ እውነት ሁሉ ይመራናል። የእግዚአብሔርም ቃል እውነት ነው፡ ቃልም ክርስቶስ ነው፡ "እኔ መንገድ፡ እውነት፡ እና ሕይወት ነኝ።" እርሱ ቃል ነው፡ "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ቃልም ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ።" ከዚያም እውነተኛውን

መሪ፡ መንፈስ ቅዱስን ከተከተልን፡ ያየውን፡ የሰማውን፡ ሊነግረን እና ሊመጣ ያለውን ነገር ሊያሳየን ነው። አሜን። እዛጋ እናንተ። ወደፊት ሊመጡ ያሉ ነገሮችን ያሳያችኋል።

34 እና ዛሬ አብያተ ክርስቲያናት ያንን ሲቃወሙ፡ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደምንሄድ እንዴት መጠበቅ እንችላለን? መንፈስ ቅዱስ ሊመራን ወደ እኛ በተላከ ጊዜ፡ አንዳንድ ካህናችን፡ አንዳንድ ቢሾፖችን፡ አንዳንድ ጠቅላይ የበላይ ተመልካቾችን፡ ወይም እንደዚህ ያለ ሰው እንዲመራን እንወስዳለን፡ ያንን የሚናደርገው መንፈስ ቅዱስ እንዲመራን በተሰጠን ጊዜ ነው።

35 መንፈስ ቅዱስም ሁልጊዜ ስለ ቃሉ ይናገራል። "የምነግራችሁ ብዙ ነገሮች አሉኝ፡ አሁን ልትረዱት አትችሉም፡ እሱ ሲመጣ ግን፡ ወደ እሱ ይመራችኋል።" የማኅተሞቹ መምጣት ምክንያት ለዚህም ነው። የሰባተኛው ማኅተም ሲፈጸም፡ እግዚአብሔር ማን እንደ ሆነ፡ ምን እንደሆነ፡ እንዴት እንደሚኖር፡ ተፈጥሮውን ማንነቱን ለማወቅ፡ የእግዚአብሔር ምሥጢር፡ ሊፈጸም ይገባዋል። እስከዚያ ድረስ ሙሉ በሙሉ **እዚህ** ላይ መሆን አለባችሁ፡ አያችሁ፡ በክርስቶስ ደም የታጠበች ቤተክርስቲያንን፡ የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆችን ወደ ሙሉ ቁመና አመጣን፡ ያ ያለ ገንዘብ የተገዛው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተከፈለ ነው።

36 አሁን፡ እዚህ እኛ፡ መሪ፡ እና እሱ ከእግዚአብሔር የተገኘ መሪ ነው። አሁን፡ እኛ በምድረ በዳ ውስጥ እየሄድን ነው፡ እና የሆነ ቦታ በመንገዳችን ላይ ነን፡ እና ያለዚህ መሪ መግባባት አንችልም። እና ማንም የሚደፍር ካለ ሌላ መሪ ለመተካት ይሞክር! ካደረጋችሁ፡ እሱ ከመሰመሩ ያነሳችሁዋል። ይህ መሪ መንገዱን ያውቃል! የመንገዱን እያንዳንዱን ኢንች ያውቃል። በልብህ ውስጥ ያለውን ሀሳብ ሁሉ ያውቃል። እዚህ ያላችሁትን ሁላችሁንም ያውቃል። እሱ ማን እንደሆናችሁ እና ምን እንዳደረጋችሁ፡ ስለ እናንተ ሁሉንም ያውቃል። እርሱ የእግዚአብሔር መሪ፡ መንፈስ ቅዱስ ነው፡ እና ነገሮችን ይገልጥላችሁዋል፡ የሰማውንም ይናገራል፡ ቃላቶቻችሁን ወዲያውኑ መድገም የተናገራችሁትንም መልሶ ሊነግራችሁ ይችላል። አሜን። ምን እንደነበራችሁ፡ ምን እንዳገኛችሁ፡ የት እንደሚትሄዱ ይናገራል። መሪ፡ ትክክለኛ መሪ፡ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችሁዋል፡ ቃሉም እውነት ነው።

37 አሁን፡ መንፈስ ቅዱስ ሰው-ሰራሽ ለሆነው ሃይማኖት፡ "አሜን፡" እንድትሉ ፈጽሞ አያደርግም። የእግዚአብሄርን ቃል ብቻ ነው ከ"አሜን" ጋር የሚያቆራኘው፡ ምክንያቱም እንዲህ ነው። መንፈስ ቅዱስ በሌላ መንገድ አይመራህም። አሁን አንግዳ ነገር፡ ሁላችንም፡ የሁላችንም ታላላቅ ቤተ እምነቶቻችን እና ነገሮች ነው፡ እኛ እያንዳንዳችን በመንፈስ ቅዱስ እንመራለን እንላለን፡ እናም በሁላችንም ውስጥ እንደ ቀንና ሌሊት የሆነ ልዩነት አለ።

38 ሐናንያ ባጠመቀው ጊዜ መንፈስ ቅዱስን የተቀበለው ታናሹ ፈሪሳዊ ጳውሎስ፡ ወደ አረብ አገር ሄዶ ሦስት ዓመት ተማረ፡ ተመለሶም፡ ለአሥራ አራት ዓመት ያህል ቤተ ክርስቲያንን ስለ ምንም ነገር አማክሮ አያውቅም፡ መጥቶም በኢየሩሳሌም የሚገኘውን የቤተ ክርስቲያን መሪ፡ ጴጥሮስን በተገናኘ ጊዜ፡ በአስተምህሮ ተስማምተው ነበሩ። ለምን? ያው መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ! ጴጥሮስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ባጠመቀበት ቦታ፡ ማንም ሳይነግረው

ጳውሎስም እንዲሁ አድርጓል። ጴጥሮስ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀትን፡ እና መቀደስን፡ እና የመሳሰሉትን ባስተማረበት ቦታ፡ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ሳያማክር፡ ተመሳሳይ ነገር አድርጓል፡ ምክንያቱም ያው መሪ ነበረ። ታዲያ ዛሬ ሰዎች እነዚህን እውነቶች ሲክዱ እንዴት መሆን እንችላለን? ጴጥሮስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ምን መሆን እንዳለበት ሲያስተምር፡ ጳውሎስም ተመሳሳይ ትምህርት ነበረው፡ ′ምክንያቱም እነሱ ተመሳሳይ መሪ ነበራቸው።

39 መመሪያው እንዱን **በዚህ** መንገድ፡ እና እንዱን **በዚያ** መንገድ፡ እና አንዱን ወደ ምስራቅ እና ሌላውን ወደ ምዕራብ አይወስዳቸውም። አያችሁ፡ እሱ አንድ ላይ ሊያቆራኛችሁ ነው። እና መንፈስ ቅዱስ በአንድነት እንዲያቆየን ከፈቀድን፡ አንድ እንሆናለን። እኛ—ዲያብሎስ ወደ ተሳሳተ መንገድ እንዲወስደን ካልፈቀድንለት፡ በአንድ መንፈስ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ወደ እውነት ሁሉ በሚመራን በእግዚአብሔር መሪ፡ አንድ ልብ፡ አንድ ሐሳብ፡ አንድ እይታ ይኖረናል። ትክክል ነው። ግን መሪውን መከተል አለባችሁ። አዎን፡ ወዳጄ።

40 ኒቆዲሞስን ተመልከቱ፡ መሪ ያስፈልገው ነበር፡ ነገር ግን ብልህ ሰው ነበር። ዕድሜው የሰማንያ ዓመት ገደማ የሆነ፡ አስተማሪ ነበር። ከፈሪሳውያን ወገን ነበር፡ ወይም—ወይም ከሳንሄድሪን ወገን፡ ምክር ቤት፡ ከአገልጋዮች ማኅበር ነበር። ከታላላቅ ሰዎቻቸው አንዱ ነበር፡ የእስራኤል አስተማሪ፡ በዚህ ረገድ አዋቂ ነበር። አስቡት፡ ዋና መምህር ነበር! አዎን፡ ሕጎቹን ያውቅ ነበር፡ ነገር ግን ዳግመኛ መወለድ ጋር ሲመጣ፡ መሪ አስፈለገው። ተርቦ ነበርና። የተለየ ነገር መኖር እንዳለበት ያውቅ ነበር። በዚያ ሌሊት ከክርስቶስ ጋር የተነጋገረው ንግግር አረጋግጦለታል። የሌሎቹም ስሜት፡ ይህንኑ አረጋግጧል፡ ነገር ግን አንዳቸውም ቢሆን እርሱ የነበረው አይነት ትልቅ—ትልቅ ድፍረት አልነበራቸውም። ከእነሱ መካከል እርሱ ወደዚያ መጥቶ ያደረገውን ሊያደርግ የሚችል ማንም አልነበረም። ሁላችሁም፡ ሰዎች፡ ኒቆዲሞስን በሌሊት በመምጣቱ ኮነኑት። እዚያ ደረሰ መጣ። ደረሴ። አንዳንድ ሰዎች ቀንም ሆነ፡ ሌሊት እንኳን እንደማይጀምሩ አውቃለሁ። ነገር ግን እዚያ ደረሰ፡ መሪም ያስፈልገው ነበር፡ እናም እንዲህ አለ፡ “መምህር፡ እኛ፡” ከሳንሄድሪን ፍርድ ቤት ነን፡ “መምህር እንደሆንክ ከእግዚአብሔር እንደመጣህ እናውቃለን።” ለምን አወቀው? በምስክር የተረጋገጠ ስለነበረ። አያችሁ፡ ይህ ዳግም ልደት ምን ማለት እንደሆነ ማወቅ ፈለገ፡ እግዚአብሔርም፡ መሪው ይህ ኢየሱስ መሆኑን ስላረጋገጠለት፡ ወደ ትክክለኛው ሄደ። የተናገረውን ተመልከቱ፡ “መምህር ሆይ፡ አንተ መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናውቃለን፡ ምክንያቱም አንተ የምታደርገውን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር፡ ማንም ሊያደርግ አይችልም።”

41 በእርሱ ውስጥ ሕያው አምላክ እንዳለ፡ ማረጋገጫ ነበር። እርሱም ሲመሰክር፡ “ሥራውን የሚሠራው እኔ አይደለሁም፡ በእኔ የሚኖረው አባቴ ነው። እውነት እላችኋለሁ፡ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም፡ ነገር ግን አብ ሲያደርግ ያየውን፡ ወልድ ደግሞ እንዲሁ ያደርጋል። አብ ይሰራል፡ እኔም እስከ አሁን እሰራለሁ።” በሌላ አነጋገር፡ እግዚአብሔር ምን ማድረግ እንዳለበት አሳየው፡ እናም ሄዶ ልክ እንዳየው አደረገው። እግዚአብሔር የሚያደርገውን እስከሚነግረው ድረስ ምንም አላደረገም። አሜን። ያ ግልጽ የሆነ እውነት ነው። ዝም ብለን ብንንቀሳቀስ እና መንፈስ እንድንሰራ እስኪያነሳሳን ድረስ

ብንጠብቅ! ያ ነው በቃ። እናም በክርስቶስ ሙሉ በሙሉ የጠፋችሁ ሁኑ እናም እኔን እንደሚያደርግ እናንተንም ሊሽልታችሁ አይገባም፡ ነገር ግን ጭንቅላቱ በመጀመሪያ ትንሽ ሲያወዛውዝላችሁ፡ ዝግጁ ትሆናላችሁ ምንም የሚያግዳችሁ ነገር የለም፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ ታውቃላችሁና።

42 መሪ ያስፈልገው ነበር። እሱ የተረጋገጠለት መሪ ነበር። እሱ በዚህ መሪ ሊመራ ይችላል ምክንያቱም ይህ መሪ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተገኘ መሆኑን ስለሚያውቅ ነው። ባገለገለው ወግ፡ ምናልባት በፈሪሳውያንና፡ በሰዱቃውያን፡ ሌላም በማናቸውም ነገር እንደ ሆነ አውቋል፡ በእነዚያ ሃይማኖቶች በሙሉ ብያገለግልም ምንም ኣዲስ ነገር ሲከሰት አላየም። እነሆን አንድ ሰው ወደ ትዕይንቱ እንዲህ እያለ መጣ፡ እርሱም ተሰፋ የተሰጠበት የመጽሐፍ ቅዱስ መሲሕ ነው። ዘወርም ብሎ የእግዚአብሔርን ሥራ ይሠራል። ኢየሱስም፡ "የአባቴን ሥራ ካላደረግሁ፡ አትመኑኝ። እኔን ካላመናችሁ፡ ግን እኔ የማደርገውን ሥራ እመኑ፡ እነርሱ ስለ እኔ ይመሰክራሉ።"

43 ያኔ፡ ኒቆዲሞስ እንዲህ አለ፡ "መምህር ሆይ፡ አንተ የምታደርገውን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ካልሆነ ማንም ሊያደርግ አይችልምና፡ መምህር እንደሆንክ እናውቃለን።" ተመልከት፡ እሱ የነገሩ ባለቤት ቢሆንም፡ መሪ ያስፈለጌው ነበር። የቤተክርስቲያኑ መምህር ነበር። ክብር ነበረው፡ እርሱ—ታዋቂ ቦታዎች ነበሩት፡ ታላቅም ሰው ነበር፣ ምንም ጥርጥር የለውም፡ በሀገሪቱ በኩል ከሰዎች ሁሉ አክብሮት ነበረው። ዳግመኛ ወደ መወለድ ሲመጣ ግን፡ መሪ አስፈለገው! ስለዚህ እኛም፡ አዎ፡ መሪ ያስፈልገናል።

44 ቆርኔሌዎስ፡ ታላቅ ሰው፡ የተከበረ ሰው ነበር። አብያተ ክርስቲያናትን ሠራ። አይሁድ ሃይማኖታቸው ትክክል እንደሆነ ስለሚያውቅ ያከብራቸው ነበር። ምጽዋትም ከፍሎ፡ በየዕለቱ ይጸልይ ነበር፡ መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ ግን (በቤተክርስቲያን ውስጥ አንድ ነገር ተጨምሯል)፡ መሪ አስፈለገው። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ላከለት። በጴጥሮስ በሚባል ሰው ላከው፡ "ጴጥሮስ ይህን ቃል ገና ሲናገር፡ መንፈስ ቅዱስ በላዩ ወረደ።" [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] እግዚአብሔር መሪውን በጴጥሮስ በኩል ተጠቅሟል። ቆርኔሌዎስንም ወደ ትክክለኛው መንገድ ስለመራው፡ተጠቅሞበታል። እርሱም ገና ሲናገር፡ መንፈስ ቅዱስ በአሕዛብ ላይ ወረደባቸው። ከዚያም እንዲህ አለ፡ "እነዚህ እንዳይጠመቁ፡ ውኃን የሚከለክላቸው ማነው?" እያችሁ፡ አሁንም መሪው እየተናገረ ነው እንጂ፡ ጴጥሮስ አይደለም። ምክንያቱም እነዚያ፡ የአይሁድ... ማለቴ የአሕዛብ ስብሰብ ናቸው፡ ለእሱም "ርኩሳን፡ የቆሸሹ" ናቸውና መሄድ እንኳን አልፈለገም ነበር። መሪው ግን እንዲህ አለ፡ "እልክሃለሁ።" መሪው ሙሉ በሙሉ ሲቆጣጠራችሁ፡ እንዲመራችሁ ስትፈቅዱለት፡ አደርጋለው ብላችሁ የማታስቡትን ነገር ታደርጋላችሁ። ኦህ፡ በመንፈስ ቅዱስ መመራት እንዴት ድንቅ ነው። መሪው እሱ ነው። ደህና። በጴጥሮስ በኩል ተናግሮ ምን ማድረግ እንዳለበት ነገረው። ከዚያም ሁሉም መንፈስ ቅዱስን በተቀበሉ ጊዜ፡ እንደዚህ አለ፡ "እንደ እኛ በመጀመሪያ ላይ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ እያየን፡ ውሃን ልንከለክላቸው አንችልም።" እናም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጠመቋቸው። አሁን፡ ይህን እንዲያደርግ ማን መራው? በእሱ ውስጥ የነበረው መሪ። ኢየሱስ እንደዚህ አላላቸውምን፡ "ስለ ምትናገሩት አትጨነቁ፡ የምትናገሩት እናንተ

አይደላችሁምና፡ በእናንተ የሚኖረው አብ ነው፡ እርሱ ይናገራል”? አሜን።

45 ጃንደረባው፡ ከኢየሩሳሌም ሲመጣ። እግዚአብሔርም በዚያን ጊዜ በዓለም ውስጥ መሪ ነበረው፡ መንፈስ ቅዱስ፡ እና በዚህ መሪ የተሞላ አንድ ሰው እዚያ ነበረው። እሱ እንኳን ሰባኪ አልነበረም፡ እንደ ዲያቆን አይነት ነበር። በዚያም ድውያንን እየፈወሰ አጋንንትንም እያወጣ ነበር፡ ታላቅ ሁከትንም አስነሳ፡ በከተማይቱም ታላቅ ደስታ ሆነ። በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በዙሪያው እንዲሰበሰቡ አድርጓል፡ እና መሪው እንዲህ አለ፡ “ይህ በጣም በቂ ነው፡ በዚህ መንገድ እንመለስ።” ከመሪው ጋር አልተከራከረም።

46 መሪያችሁን ቃል በጭራሽ አትከራከሩት። ተከተሉት። ይሄን ካላደረጋችሁ፡ ጠፍታችሁ ትገኛላችሁ። እና፡ አስታውሱ፡ እሱን ስትተዉት፡ እናንተ ብቻ ትሆናላችሁ፡ ስለዚህ ወደ መሪው መቅረብ እንፈልጋለን።

47 ስለዚህ በመንገድ ላይ፡ እንዲህ አለ፡ “ፊልጶስ ሆይ፡ ይህን ስብሰብ አሁን ተወውና፡ ማንም ወደሌለበት በረሃ ውጣ። እኔ ግን ወደዚያ እልክሃለሁ፡ አንተንም ወደዚያ በላኩህ ጊዜ የሆነ ሰው ይኖራል።” እነሆም በኢትዮጵያ ላለችው ንግሥት ታላቅ ሰው የነበረ፡ ብቸኛ ጃንደረባ መጣ። ስለዚህም የኢሳይያስን መጽሐፍ እያነበበ፡ ይጓዝ ነበርና። መሪውም እንዲህ አለ፡ “ወደ ሰረገላው ቅረብ።”

እርሱም “የምታነበው ይገባሃልን፡” አለው?

48 እንደዚህ አለ፡ “የሚመራኝ ሰው ሳይኖር እንዴት ይገባኛል?” ኦህ፡ ይገርማል! ፊልጶስ ግን መሪ ነበረው። አሜን። ከዚያው መጽሐፍ ጀምሮ፡ ክርስቶስን ሰበከለት። አሜን። መሪው! ስለ ኃይማኖት መግለጫ አልተናገረውም፡ የተናገረው ስለ መሪው ነው፡ ስለ ክርስቶስ! በዚያም በውኃ አጠመቀው። በእርግጥ፡ እንደዛ ነበር። ኦህ፡ እንዴት ደስ ይላል!

49 በዘጸአት 13፡21፡ ላይ እስራኤል ከግብፅ ወጥተው ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲሄዱ፡ ከዚህ በፊት በዚያ መንገድ ተጉዘው እንደማያውቁ እግዚአብሔር ያውቃል። አርባ ማይል ብቻ ነበር፡ ነገር ግን ከእነሱ ጋር የሚሄድ ነገር ያስፈልጋቸው ነበር። መንገዳቸውን ያጡ ነበር። ስለዚህም እርሱ፡ እግዚአብሔር፡ መሪ ላካቸው። ኦሪት ዘጸአት 13፡21፡ ይህን የሚመስል ነገር፡ “በመንገድ ይጠብቅህ ዘንድ፡ የእሳት ዓምድ፡ መልአኬን በፊትህ እሰድዳለሁ።” ወደዚች ወደ ተስፋይቱ ምድር ሊመራቸው። የእስራኤልም ልጆች ያንን መሪ፡ የእሳት ዓምድ (በሌሊት)፡ በቀን ደመና ተከተሉ። ሲቆም፡ እነሱም ይቆማሉ፡ በተጓዘ ጊዜ፡ እነሱም ይጓዙ ነበር። ወደ ተስፋይቱ ምድርም ባስጠጋቸው ጊዜ፡ ለመሻገር ብቁ አልነበሩምና፡ መልሶ ወደ ምድረ በዳ መራቸው። ከእነርሱ ጋር አይሄድም ነበር።

50 ዛሬ ያለችው ቤተ ክርስቲያንም፡ እንደዝሁ ነች። ዛሬም የእግዚአብሔር ትዕግሥት፡ በኖኅ ዘመን እንደነበረው እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ ብትታረምና ብትስተካከል ኖሮ ድሮ በተወሰደች ነበርና። እርሱ ግን ደጋግሞ ደጋግሞ ደጋግሞ ሊመራን ተገባው።

51 እስራኤላውያን የግብፅን የሞቱ ወታደሮች፡ የሰጠሙ ፈረሶች፡ አይተው እልል ሲሉ፡ የፈርዖን ሰረገሎች፡ ተገልብጠው ሲያዩ፡ ድል ሲያደርጉ ገና አልገባቸውም፡ ሙሴ በመንፈስ፡ በመንፈስ ሲዘምር፡ ማርያም በመንፈስ

ስትጨፍር፡ የእስራኤልም ሴቶች ልጆች እልል ሲሉ እየጨፈሩ፡ ወደ ዳርቻ እየሮጡ ሲወርዱ፡ ከወተት እና ከማር ጥቂት ቀናት ብቻ ርቀው ነበሩ። አርባ አመት እንደቀረው ግን አላወቁም ነበር፡ ምክንያቱም በእግዚአብሔር እና በመሪው ላይ ማጉረምረም ጀመሩ።

52 እና እራሳችንን በተመሳሳይ መንገድ እናገኛለን። ከዚህ በኋላ ወደ ሽሬቬፖርት እሄዳለሁ። እናም መንፈስ ቅዱስ በምስጋና ቀን ወረደ፡ ከሃምሳ አመት በፊት፡ በ—በሉዊዚያና፡ በምስጋና ቀን። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቤተክርስቲያን እንዴት ወደቀች! የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ ላይ የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን እንደነበረች ታውቃላችሁ? ያ እውነቱ ነው። ትክክል ነው። የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ነበረች፡ ነገር ግን የተከበሩ ሹማምንቶች ገብተው የ—የእግዚአብሔርን መጻሕፍት ወደ ወጋቸው መለወጥ ይጀምራሉ፡ ህጎችን እና የመሳሰሉትን፡ ይጨምሩበታል። አሁንም ምን እንዳገኙ ተመልከቱ፡ በማናቸውም የቅዱሳት መጻሕፍት ቅንጣት አይደለም። የመንፈስ ቅዱስ ቁራሽ አንጀራ፡ በሌላ ነገር ተክተዋል። በመጥለቅ ፈንታ መርጨትን ተክተዋል። "ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን" በ"አብ፡ ወልድ፡ እና መንፈስ ቅዱስ" ተክተዋል። በእኛ ላይ የተቀመጡትን የእግዚአብሔርን ታላላቅ ህጎችን ሁሉ ተክተውልናል፡ እና እነሱ ከቅዱሳት መጻሕፍት ኣስተምህሮ ርቀው፡ ርቀው፡ ርቀው ይገኛሉ።

53 ከሃምሳ ዓመታት በፊት ጴንጤቆስጤም፡ በሉዊዚያና ወደቀ፡ እና ሌላ ሁለት መቶ ዓመታት ከቆየ፡ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ይልቅ የባሰ ይሆናል፡ ባለፉት ሃምሳ ዓመታት ውስጥ በነበረበት መንገድ መውደቁን ከቀጠለ፡ ምክንያቱም ያለማቋረጥ፡ በየጊዜው እየጨመሩበት ነውና። የድሮ-ዘመን ሰባኪዎች ጠፍተዋል። የጎዳና ላይ ስብሰባዎች፡ አንድም በጭራሽ አትሰሙም። አሁን ያለው ሁሉ የሆሊውድ ሰብሰብ የጨመረብን፡ ራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ ፀጉራቸውን-የሚያሳጥሩ፡ ቁምጣ የሚለበሱ ሴቶች፡ መዋብያዎች የሚቀባቡ፡ እና ሌሎችንም ሁሉ ብቻ ነው። አንዳንድ እፍላዎች በጊታር፡ በየሜዳው ወደላይ እና ወደ ታች ይዘላሉ፡ እና ሴቶች እንደ... ልክ እንደ ተወጠረ ቆዳ—ከሞላ ጎደል፡ ሰውነታቸው ውጭ ነው፡ መድረኩ ላይ እየተቀሳቀሱ፡ መድረኩን ወደላይ እና ወደ ታች መሮጥ፡ ጆሮ ጌጥ ተንጠልጥሎ መደነስ፡ እና ከእነዚህ ውስጥ አንዱ እዚህ አዳዲስ የምድሪቱ-የሴት-ፀጉር-አቆራረጥ፡ ከዚያም እራሱን ክርስትና ብለው መጥራት።

54 የሚያስፈልገን የድሮ ዘመን፡ ከእግዚአብሔር-የተላከ፡ ያንን ዓለማዊነት ከቤተ ክርስቲያን የሚያቃጥል የተቀጣጠለ ሃይማኖት ነው። ወደ መንፈስ ቅዱስ እና እሳት መመለስ አለብን፡ ዝገትን ወደሚያቃጥለው፡ የድሮውን-ስብከት ወደሚመልስ፡ መንግሥተ ሰማያትን ከፍ ወደሚያደርግ፡ እና ሲኦልን ወደ ሚያተኩስ፡ አፈ-ሙዝን ቀጥ ወደሚያደርግ ነገር መመለስ አለብን። እንዲህ ዓይነት ስብከት ያስፈልገናል። ግን ዛሬም ታደርጉታላችሁ፡ ጉባኤያችሁ ለእናንተ ድምጽ ይሰጣችኋል።

55 አንዳንድ ጊዜ ጥሩ ሰባኪዎች በጉባኤያቸው ይመራሉ። እኔ ምንም አይነት ድርጅት የለለኝ ለዛ ነው። አንድ ዋና መሥሪያ ቤት አለኝ፡ ያ ከሰማይ ነው። የትም ቢልከኝ፡ እዛ እሄዳለሁ። እሱ የሚናገረውን ሁሉ፡ እኔ እናገራለው። ተቋም አንፈልግም። ይህች ቤተክርስቲያን ስለ ሃይማኖት ተቋም ማውራት በጀመረች

ጊዜ፡ ያኔ ፓስተራችሁን አጥታችሁዋል። አንድ አምስት-ደቂቃ እንኳን፡ ስለ እርሱ አናወራም። ወደ ተቁም የተቀየረ እያንዳንዱ ቤተ ክርስትያን ከጥቅም ዉጪ ሆነዋል፡ እናም እንደዛ ያልሆነች አንድ ካለች ንገሩኝ፡ እንደገና የተነሳ ካለም ንገሩኝ። ቤተ ክርስቲያንን እንዲመራ የተላከው መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ፡ የተወሰኑ ሰዎች አይደሉም። መንፈስ ቅዱስ ባለ ሙሉ-ጥበብ ነው። ሰዎች ኮሩዎች፡ ግዴለሽ ይሆናሉ።

56 እግዚአብሔር መሪ እንደሚልክላቸው፡ በመንገዳቸውም እንደሚመራቸው ነግሯቸው ነበር። እና ያንን የእሳት ዓምድ እስከተከተሉ ድረስ፡ የተጠበቁ ነበሩ። ወደ ተስፋይቱ ምድር በር ድረስ መራቸው፡ ያም እሱ መሄድ የሚችልበት ድረስ ነበር። ከዚያም ያ ታላቅ እርበኛ፡ ኢያሱ፡ የተናገራቸውን ቀን አስቡ፡ “ራሳችሁን ቀድሱ፡ በሦስተኛው ቀን እግዚአብሔር ዮርዳኖስን በዚህ ይከፍላል እኛም እንሻገራለን።”? አሁን በመጽሓፍ ቅዱስ ያለውን ተመልከቱ (ይሄኛውን ደስ ይለኛል)፡ እንደዚህ አለ፡ “ከዚህ በፊት በዚህ መንገድ አላለፋችሁበትምና፡ ከታቦቱ ጀርባ ቆዩ።”

57 ታቦቱ ምን ነበር? ቃሉ። የኃይማኖታዊ ተቋማት መንገዶቻችሁን አሁን አትጓዙ፡ ከቃሉ ጀርባ ቆዩ፡ ምክንያቱም ከዚህ በፊት በዚህ መንገድ አልሄዳችሁበትምና። እናም፡ ወንድሜ፡ የክርስቲያን ቤተክርስቲያን እራሷን መመርመር ያለባት ጊዜ ቢኖር፡ አሁን ነው። እኛ አሁን ባለንበት በሮም ይህ ታላቅ ሰብሰባ እየተካሄደ ባለበት፡ ልዩነቶች እየተፈጠሩ ነው፡ የአብያተ ክርስቲያናት ሕብረት፡ የአውሬውን ምስል ለማድረግ እነዚህ ሁሉ የሃይማኖት ተቋማት በአንድነት ሲዋሐዱ፡ ልክ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ነው የሆነው። እና ዛሬ ጠዋት በመልእክቶች ውስጥ የተናገርነውን ታውቃላችሁ። እና እኛ እዚህ ነን፡ ሁሉም ነገር ልክ በበሩ ላይ ነው፡ እና ሰዎች አሁንም ከሃይማኖት በኋላ ይከተላሉ። ከቃሉ ጀርባ ብትቆዩ ይሻላቿል! ቃሉ ይመራችኋል፡ ምክንያቱም ቃሉ ክርስቶስ ነውና፡ ክርስቶስም እግዚአብሔር ነውና፡ እግዚአብሔርም መንፈስ ቅዱስ ነውና።

58 ከቃሉ ጀርባ ቆዩ! ኦህ፡ አዎን፡ ዋዳጄ! ከዚያ መሪ ጋር ቆዩ። ከኋላው ቆዩ። ከፊት ለፊቱ አትዉጡ፡ ከኋላው ቆዩ። እናንተ ለመምራት እንዳትሞክሩ፡ እንዲመራችሁ ፍቀዱለት። ይምራችሁ ተዉት።

59 ኢያሱም አለ፡ “አሁን፡ ከዚህ በፊት በዚህ መንገድ አልፋችሁ አታውቁም፡ ስለ መንገዱ ምንም የምታውቁት ነገር የለም።”

60 የዛሬውም ችግር ያ ነው። ወደ ሰፊው መንገድ እንዲመራችሁ ምንም መሪ አያስፈልጋችሁም። ኦህ፡ ሁሉንም አቋራጭ መንገዶች እና ሌሎች ነገሮችን ሁሉ ታውቃላችሁ። የኃጢአትን መንገድ ሁሉ ታውቃላችሁ። የለም... ኦህ፡ ለረጅም ጊዜ ኖራቿል። ሁሉንም አቋራጭ እንደሚታውቁት፡ ማንም ሊነግሯችሁ መሞከር የለበትም። ያ ትክክል ነው፡ ስለ እያንዳንዱ ኃጢአት፡ ሁሉንም ታውቃላችሁ። ማንም ሰው እንዴት እንደሚሰረቅ ሊነግራችሁ አይገባም፡ እናንተ ታውቃላችሁ። ማንም ሰው እንዲህ ርገሙ ብሎ ሊነግራችሁ አይገባም፡ እናንተ ታውቃላችሁ። ማንም ሰው እነዚህን ክፋ ነገሮች እንዴት ማድረግ እንዳለባችሁ ሊነግራችሁ አይገባም፡ ምክንያቱም በሁሉም ቦታ በሁሉም ዛፎች ላይ ተለጥፏል።

61 ነገር ግን፡ እናንተ ክርስቲያኖች የሆናችሁ ሰዎች፡ መሻገራችሁን፡ አስታውሱ። ወደ ሌላ ምድር ገብታቿል። እንደገና ተወልዳቿል። እናንተ ያላችሁበት ምድር፡ በሰማያዊ ምድር ውስጥ ናችሁ። በተስፋይቱ ምድር ውስጥ ናችሁ።

62 አካባቢያችሁን ታውቃላችሁ፡ ማየት ትችላላችሁ። አዎን፡ ኦህ፡ ይገርማል። ካርታ እንዴት መያዝ እንዳለባችሁ፡ ምንና—ምን ታውቃላችሁ። ዳይስ ምን እንደሆነ፡ ሲሽከረከር፡ ምን ማለት እንደሆነ፡ እና እንደዛ ያለውን ነገር ሁሉ ታውቃላችሁ። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቅድስናና ጽድቅ እንዲሁም ኃይሉ፡ እና መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደሚሰራ እና ምን እንደሚሰራ፡ ወደ ማወቅ ስትደርሱ ከመሪው፡ ከቃሉ ጀርባ ብትቆዩ ይሻላቿል። አያችሁ? ከዚህ በፊት በዚህ መንገድ አልፋችሁ አታውቁም።

63 ደህና፡ እንደዚህ ትላላችሁ፡ "እኔ ቆንጆ ብልህ ሰው ነበርኩኝ—ኮሌጅ ውስጥ ሁለት ዲግሪ ነበረኝ።" ብትረሳው ይሻላል። አዎን፡ ዎዳጄ።.

64 "በሴሚናሪ ውስጥ አልፈናል።" ብትረሱት ይሻላል። አዎ። ከመሪው ጀርባ ብትቆዩ ይሻላቿል። እንዲመራችሁ ፍቀዱለት። እሱ መንገዱን ያውቃል፡ እናንተ አታውቁም። ከዚህ በፊት በዚህ መንገድ አላለፋችሁም። "ደህና፡" "እነርሱ አላቸው፡" ትላላችሁ።

65 ካላቸው ተመልከቱ። ኢየሱስም፡ "በዚህ መንገድ ያለፉ፡ እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል። በስሜ፡ አጋንንትን ያወጣሉ፡ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፡ ወይም እባቦችን ቢይዙ ወይም ገዳይ ነገሮችን ቢጠጡ፡ ምንም አይጎዳቸውም። እጃቸውን በሕሙማን ላይ ቢጭኑ፡ ይድናሉ።" አብዛኞቻቸው እምቢ ይላሉ፡ ይክዱታል፡ በምሪት እንኳን አይደለም ይላሉ። መሪውን እየተከተሉ አይደሉም። ሰው-ሰራሽ ሃይማኖት እየተከተሉ ነው። ታውቃለችሁ፡ በዚህ መንገድ ስላላለፋችሁ፡ ከቃሉ ጀርባ ብትቆዩ ይሻላቿል።

66 ነገር ግን ዳግመኛ ተወልዳቿል፡ እናም በቅድስና ተወልዳቿል። ከዚህ በፊት በዚህ መንገድ አላለፋችሁም። በዚህ መንገድ ካ-... በዚህ መንገድ ካለፋችሁ፡ በቅድስና መምጣት አለባችሁ፡ ምክንያቱም አዲስ ምድር ነውና፡ አዲስ ሕይወት፡ አዲስ ሕዝብ ነው።

67 ወደ ቤተክርስቲያን ስትመጡ፡ አንድ ሰው ተነስቶ "ክብር ለእግዚአብሔር! ሃሌ ሉያ!" ሲል ሲጮህ ትሰማላችሁ፡

68 እናንተ ግን፡ እንዲህ ትላላችሁ፡ "በጣም፡ ይገርማል፡ በቤተክርስቲያናችን እንዲህ አድርገው አያውቁም! ተነስቼ እወጣለሁ!" ኧም-ሃም። አያችሁ? ተጠንቀቁ።

69 አሁን፡ ከቃሉ ጀርባ ቆዩ፡ መሪው ይምራችሁ። "እርሱ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፡ እና ሰለ እናንተ ሰለነገርኳችሁ ነገር ይገልጥላቿል። እሱ ያንን ያሳያቿል። እሱ ሊመጣ ያለውን ነገር ይነግራቿል፡" እውነተኛ መሪ። ወደ ጳጳሱ አትሂዱ፡ ወደ መሪው ሂዱ። ከመሪው በስተቀር ወደ ማንም አትሂዱ። ሊመራችሁ የተላከው እርሱ ነው። እሱ የሚያደርገው ያንን ነው። እግዚአብሔር መሪ አቅርቦላቿል። እግዚአብሔር የዘጋጀውን መንገድ ያዙ።

70 የዛሬው ችግር፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡ ሰዎች ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ተቀምጠው፡ ያልለመዱት ነገር ይሆንባቸዋል።

71 አንድ ከተለመደው ቤተክርስቲያን የመጣችውን ትንሿን ሴት አደንቃታለው፡ ለሷ ብቻ ፀሎት አድርጌ ነበር። እግዚአብሔር ትንሿን ሴት ሊፈውሳት ነው። እሷ ይህ አልገባትም። ስለ ጉዳዩ ምንም የምታውቀው ነገር የለም። ገባችና፡ እንደማታውቅ ተናገረች። እኔ ግን "ነይና አነጋግሪኝ፡" አልኳት። እሷ ዓይናፋር እና ኋላ ቀር ነበረች፡ ግን መሪው ደጋግሞ "ቀጥይ" ይላት ነበር። ተረዳችው። ያ ነው በቃ። እያችሁ፡ ወደ እነዚህ ነገሮች የምንመራው በመንፈስ ቅዱስ ምክንያት ነው። እያችሁ፡ እግዚአብሔር የተዘጋጀ መንገድ አለው።

72 መቼስ ታውቃላችሁ... የዱር ዝይዎች ሲሻገሩ፡ ዳክዬዎቹ ወደ ደቡብ ሲሄዱ አስተውላችኋል? መልካም፡ አሁን አስታውሱ፡ ያ ትንሽ ምስኪን ዳክዬ በአንድ ቦታ በኩሬ ውስጥ ተወለደ። ምስራቅ፡ ሰሜን፡ ምዕራብ፡ እና ደቡብ የቱ ጋር እንደሆነ አያውቅም። ኩሬው ካናዳ ውስጥ በተራሮች ላይ እንደሚኖር በስተቀር ምንም የሚያውቀው ነገር የለም። ከዚያ ከኩሬው ወጣ ብሎ አያውቅም፡ ነገር ግን መሪ ሆኖ ነው የተወለደው። ያ ትንሽ ተባእት ዳክዬ መሪ ለመሆን ተወለደ። እና የመጀመሪያው ነገር፡ አንድ ምሽት አንድ ትልቅ በረዶ ከተራሮች እናት ላይ ይወርዳል። ምን ተፈጠረ? ያ ቀዝቃዛ ነፋስ እዚያ እሱ ባለበት በኩል ነፈሰ። ሲንቀጠቀጥ መገመት እችላለሁ፡ እንዲህ ሲል፡ "እማዬ፡ ይህ ምን ማለት ነው?" እያችሁ፡ ከዚህ በፊት ያን ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ ተሰምቶት አያውቅም። ዙሪያውን ማስተዋል ይጀምራል፡ የኩሬው ጠርዝ ዙሪያ ማስተዋል ይጀምራል፡ መቀዝቀዝ ይጀምራል፡ በኩሬው ላይ በረዶ ይመጣል። እሱ አያውቅም፡ ግን በድንገት... ለዚያ የዳክዬ መንጋ መሪ ለመሆን ተወለደ። ሲነፍስበት በኩሬው መካከል በትክክል ይዘላል። የምትፈልጉትን ትሉታላችሁ። ምሪት ብለን እንጠራዋለን፡ ወይም ኦህ፡ በደመ ነፍስ ነው፡ ልትሉት ትችላላችሁ፡ ምንም ይሁን። እሱ ወዲያውኑ ከኩሬው መሃል ይወጣና፡ ትንሿን ጩኸት በአየር ላይ አጥብቆ ይጮሃል፡ እናም ይሄድና፡ "ሆንክ-ሆንክ፡ ሆንክ-ሆንክ!" እና በኩሬው ላይ ያለ እያንዳንዱ ዳክዬ ወደ እሱ ይመጣል። ለምን? ልክ እሱ በሚጮኽበት መንገድ፡ መሪያቸውን ያውቃሉ።

73 "መለከት የማይታወቅ ድምፅ ቢሰጥ፡ ለጦርነት ማን ሊዘጋጅ ይችላል?" ትክክል ነው።. መለከት የማይታወቅ ድምፅ ቢሰጥ ለጦርነት ራሱን የሚያዘጋጅ ማን ነው?

74 ደህና፡ ያ ትንሽ ዳክዬ እርግጠኛ ያልሆነ ድምጽ ከሰጠ፡ እራሱን ለበረራ ማን ያዘጋጃል? ያ ትንሽ ምስኪን ዳክዬ እዚያ ላይ ትንሹን መንቆር ይዘረጋና፡ ይጮሃል፡ "ሆንክ-ሆንክ፡ ሆንክ-ሆንክ!" እና እያንዳንዱ ዳክዬ ወደ እሱ ይመጣል። "ሆንክ-ሆንክ፡ ሆንክ-ሆንክ!" እዚህ ናቸው። እንዲህ ዓይነቱ ኢዮቤልዩ፡ እዚያው በኩሬው መሃል ላይ ይኖራቸዋል፡ በተደጋጋሚ መዞር እና መዞር እና መዞር ነው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሁሉም ነገር በእሱ ላይ እንደሚንቀሳቀስ ይሰማዋል፡ ያንን መልቀቅ አለበት። ትንንሽ ክንፎቹን ዘርግቶ ኩሬውን ትቶ ይበርራል፡ በአየር ላይ ተነስቶ አራት ወይም አምስት ጊዜ ይዞራል፡ እና ልክ እሱ መሄድ በሚችልቤ በቀጥታ ወደ ሉዊዚያና ይሄዳል፡ ሁሉም ዳክዬዮቹ ወዲያው ከኋላው ይሆናሉ። "ሆክ-ሆንክ፡ ሆንክ-ሆንክ፡" እዚህ ይመጣል። ለምን? እሱ መሪ ነው! አሜን! ዳክዬዎች መሪያቸውን ያውቃሉ፡ ቤተክርስቲያን አታውቅም። እዎ፡ ምን ማድረግ እንዳለበት ያውቃል።

75 ምስኪን ዝይዎችን ተመልከቷቸው፡ ከአላስካ ተነስተው። አሁን፡ አንድ

ምስኪን ዝይ ሁል ጊዜ ይመራቸዋል፡ እና ዝይዎቹ ያንን ወንድ ዝይ ከሚገባው በላይ መመልከት አለባቸው። ያ ወንድ ዝይ የሚናገረውን ማወቅ አለባቸው። የዛሬ አራት አመት አካባቢ **በሉክ** መጽሔት ላይ እንብባችሁ ታውቃላችሁ፡ የሚሰራውን የማያውቅ አንድ ምስኪን ዝይ ነበረ የሚለውን እንብባችሁታል? ብዙ ዝይዎችን ወደ እንግሊዝ ድረስ መራቸው። ያ ትክክል ነው። ከዚህ በፊት እንግሊዝ ገብተው አያውቁም ነበር። ለምን? እነሱ መ—መሪያቸውን ፈጽመው አስተውለውት አያውቁም። ያ ምስኪን ወንድ ዝይ ወዴት እንደሚሄድ አያውቅም ነበር። እና አሁን እዚያ ይኖራሉ እና ተመልሰው መመለስ አይችሉም።

76 ዛሬ በአጠቃላይ የእነዚህ ዝይዎች ጉዳይ ያ ነው፡ አሁንም ይጎርፋሉ። **የሉክ** ጋዜጣ እንዳለው፡ እነዚህ ዝይዎች በእንግሊዝ ዙርያ ይበርራሉ፡ እንዴት እንደሚመለሱ ግን አያውቁም፡ ብለዋቸዋል። እኔ የማውቃቸው አንዳንድ **ዝይዎች** እንደዚሁ ናቸው። መንጋ አላችሁ፡ እና ትልቅ የሚቆይ ሰብሰባ አላችሁ፡ እና አንዳንድ ተሀድሶ አራማጆች አብሯችሁ መጥተው ለጥቂት ጊዜ ይሰብካሉ፡ ግን ወዴት እንደምትሄዱ አታውቅም። በየዙሪያው እና በየአካባቢው ትጨናነቃላችሁ፡ ምክንያቱም ወደ ሃይማኖት ተቋም የሚመራችሁ ዝይ ስላላችሁ፡ እና ወደ እግዚአብሔር ቃል፡ ወደ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አትመለሱም። እና ለምን በዘመናችን መነቃቃት እንዳላገኘን እንገረማለን። ኧሃ-ሃም። አያችሁ? ያንን የተረጋገጠ ድምጽ ማግኘት አለባችሁ! ያ ድምፅ ወንጌልን የሚተነፍስ የወንጌል መለከት ነው፡ የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ ነው። የኃይማኖት መግለጫ ሳይሆን፡ የሃይማኖት ተቋም ሳይሆን፡ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ፡ መንፈስ ቅዱስ ነው። "ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል።" አያችሁ? እና እዚያ በመንገድ ላይ ይሄዳሉ።

77 አንድ ጊዜ አንድ ምስኪን ዝይ፡ በጨለማ ውስጥ ሊያበራቼው እየሞከረ፡ ብዙ ተገድለዋል፡ እሉ፡ ለራሱ ወዴት እንደሚሄድ፡ አላወቀም ነበር፡ ሁሉም እዚያ ከተራራዎች ዳር ተጋጩ፡ ከፊሎቹም ተበታተኑ፡ ተሰባበሩ። በእርግጠኝነት! ትክክለኛውን ድምፃቸውን ማወቅ ነበረባቸው። ያ ትንሽ ምስኪን ዳክዬ፡ ትክክለኛ ድምጽ ቢኖረው እና ሁሉም የሚያውቁት ቢሆን፡ ጥቂት ኢዮቤልዩ መንጋ አላቸው እና ወደ ደቡብም ይሄዳሉ። ወደዚያ የሚወርዱት ለምንድነው? የማይቀዘቅዝ ቦታ ፍለጋ።

78 አሁን፡ እግዚአብሔር ቅዝቃዜን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል ለማወቅ ለዳክዬ በቂ ስሜት ከሰጠው፡ ለቤተ ክርስቲያን እንዴት ሊሰጥ ይገባው ነበር? ዳክዬ ያንን በደመ ነፍስ ማድረግ ከቻለ፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስስ? ከአሮጌ ሥርዓት እና ከሃይማኖት መግለጫዎች እና ነገሮች፡ ወደ ክብር፡ ወደሚደንቅ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሊመራን ይገባል። በጎነትን፡ እውቀትን፡ ትዕግስትን፡ እግዚአብሔርን መምሰል፡ እና መንፈስ ቅዱስን ያመጣል። እውነተኛው መሪ የሚመራው ይህንን ነው፡ ምክንያቱም እሱ ከወንጌል በስተቀር ምንም አይተነፍስም፡ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ። በእርግጥ፡ መሪ ያስፈልጋቿል!

79 መቺ፡ ጠቢባን፡ ስለ እግዚአብሔር ምንም አያውቁም ነበሩ። እነርሱ—እነርሱ አሰማተኞች፡ አሰማተኞች-ነበሩ። በምስራቅ በኩል አለፉ። ታውቃላችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ይላል፡ "ኮከቡን በምስራቅ አይተናል፡ ልንሰግድለት መጥተናል።" እነሱ ከምዕራብ ነበሩ፡ ወደ ምስራቅ ተመለከቱ እና ኮከቡን

አዩ… ወይም ወደ ምዕራብ እየተመለከቱ ነበር፡ እነሱ በምስራቅ ነበሩ። “እኛ በምስራቅ ነበርን፡ እናም በምዕራብ የእሱን ኮከብ አየን።” አያችሁ? “የሱን ኮከብ በምስራቅ አይተናል።” እና፡ አያችሁ፡ እነሱ በምስራቅ ነበሩ። “በምስራቅ ሳለን ኮከቡን አይተናል፡ እናም እርሱን ልናመልክ መጥተናል።”

80 እነዚያ ሰዎች ለመሄድ ሲዘጋጁ ሳያቸው መገመት እችላለሁ። ከባለቤታቸው አንዷ እንዲህ ስትለው ይታየኛል፡ “በል፡ ሁሉንም ነገር ተጭኗል፡ ግን ኮምፓስህ የት አለ? ” አለች፡

“አይ——በዚህ ጊዜ ኮምፓስ አልጠቀምም፡” አላት።

81 “ተራሮቹን እንዴት ሊታልፋቸው ነው? ” አለች፡ አስታውሱ፡ የጤግሮስን ወንዝ ተሻግረው በሜዳው መውረድ ነበረባቸው፡ እና… ለምን፡ በግመሎች ላይ የሁለት ዓመት ጉዞ ይጠብቃቸዋል፡ እንዴት እንዴት ያደርጉታል? “እንዴ፡ ኮምፓስ እንኳን አትወስድም፡” አለች።

“አልወስድም፡” አላት።

“እንዴት እየሄድክ ነው? ”

82 “እግዚአብሔር ባዘጋጀው መንገድ እሄዳለሁ። ያ ኮከብ ወደ ንጉሱ ሊመራኝ ነው።” ያ ነው በቃ።

83 “ኮከቡን በምስራቅ አይተናል፡ እናም እሱን ለማምለክ፡ እስከዚህ እስከ ምዕራብ ድረስ ተከትለነዋል። የት ነው ያለው? ” እነሱ የእግዚአብሔርን መንገድ ተከተሉ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ እዚያ ታች ከሃይማኖት ክምር ጋር ተያያዙት። እነዚህ ምርጥ ልብስ የለበሱ፡ ወደ ኢየሩሳሌምም ገብተው በመንገድ ላይ መውጣትና መውረድ ጀመሩ፡ እንደዚህ እያሉ፡ “ወዴት ነው? የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ” በዚያም፡ ራስ ነበረች፡ ኢየሩሳሌም ነበረች። በእርግጥ ትልልቅ ቤተ ክርስቲያኖች ስለ እሱ አንድ ነገር ማወቅ ነበረባቸው። “ወዴት ነው? የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? በምስራቅ የሱን ኮከብ አይተናል ልንሰግድለት መጥተናል። ወዴት አለ? ”

84 ለምንድነው፡ ወደ መጋቢ **አገሌ-እና-አገሌ** እና ወደ ሊቀ ካህናቱ **አገሌ-እና-አገሌ** የሄዱት፡ አንዳቸውም ስለ እሱ ምንም የሚያውቁት አልነበረም። “ለምን፡ የተወለደ የአይሁድ ንጉሥ አለ፡ እርሱ የት ነው ያለው? ” አላወቁም ነበር።

85 ነገር ግን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉ ብዙ እረኞች በኮረብታው ላይ ነበሩ፡ አዎን፡ ዎዳጄ፡ ምክንያቱም እነርሱ እግዚአብሔር ባዘጋጀው መንገድ መጥተዋልና።

86 ስለዚህ እዚያ ቆዩ፡ እና በቀጥታ እንዲህ አለ፡ “ምን ማድረግ እንዳለብን እነግራችኋለሁ፡ የቦርድ ስብሰባ ሊኖረን ይገባል።” ስለዚህ የሳንሄድሪን ሸንጎ ጠሩ፡ እና——እና ስለ እሱ የሆነ ነገር ከሰሙ ብለው አሰቡ። “አይ፡ ስለ እሱ ምንም የምናውቀው ነገር አልነበረም።”

87 ዛሬም ያለው ተመሳሳይ ነገር ነው። ስለዚህ መሪ፡ ስለሚፈውሰው፡ ስለሚሞላው፡ ስለሚያድነው፡ እንደገና ስለሚመጣው መንፈስ ቅዱስ ምንም አያውቁም። እነዚህን የሆኑ ሁሉ ነገሮችን የነገረን መሪ፡ እዚህ በመካከላቸው ነው ያለነው። የልብን አሳብ የሚያውቅ፡ ስለዚያ ምንም የሚያውቁት ነገር የለም፡

የአእምሮ ቴሌፓቲ ወይም ሌላ ነገር ብለው ይጠሩታል። ስለ እሱ ምን ማለት እንዳለባቸው አያውቁም።

88 ስለዚህ፡ አያችሁ፡ እነዚያ ጠቢባን ሰዎች፡ እስኪ... አስታውሱ፡ ኢየሩሳሌም በገቡ ጊዜ፡ ኮከቡ ጠፋ። እናም ወደ እግዚአብሔር እንዲመራችሁ ሃይማኖት መግለጫ እና የሃይማኖት ተቋም ሰውን እስከፈለጋችሁ ድረስ፡ የእግዚአብሔር እርዳታ ይተዋችኋል። ነገር ግን በታመሙና በሰለቻቸው ጊዜ፣ ጥለውአቸውም ጊዜ፣ የእነዚያን የአይሁድ እምነትና እምነት ትተው፣ ከኢየሩሳሌምም ወጡ፡ ኮከቡም እንደገና ታየ በታላቅ ደስታም ደስ አላቸው። መሪውን እንደገና አዩት! ኦህ፡ እንዴት ነው፡ ከቀደሞው ቀዝቀዝ ካለውና ከመደበኛው ቤተክርስቲያን ውጡ፡ ከዚያ ወደ ጥሩው ወደሚቀጣጠለው ተመለሱ፡ መሪውን ሲመራ አያችሁ፡ ምን አይነት ልዩነት አለው! አዎ፡ "ኮከቡን በምስራቅ አይተነው ልንሰግድለት መጥተናል።"

89 ኢያሱም አላቸው፡ "አሁን ታቦቱን ትከተላላችሁ፡ 'ምክንያቱም ከዚህ በፊት በዚህ መንገድ ሄዳችሁ አታውቁም።" እግዚአብሔር ያ ታቦት ከትክክለኛው ቦታ በሰተቀር የትም እንዲሄድ አይፈቅድም። ሁሉም ተከትለውታል፡ እናም በትክክል ዮርዳኖስን ማዶ አለፉ።

90 ዛሬም በመንፈስ ቅዱስ፡ እንዲሁ ነው። አዎን፡ ዋዳጄ። እኛ የምናውቀው ብቸኛው ነገር፡ መንፈስ ቅዱስም ይሁን ወይስ አይደለም፡ የእርሱ መግለጫ-... መገለጫዎችን እናያለን፡ መገለጫዎቹ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያረጋግጡ ናቸው።

91 አሁን፡ በቅርብ ጊዜ፡ ደም እና ዘይት የሚሉ አንዳንድ የወንድሞች ሰብሰብ ነበር፡ እንግዲህ በዚያ መንገድ ማድረግ ከፈለጉ ይሁንላቸው። ለእኔ... ያ ለእኔ ማረጋገጫ አይደለም። የቅዱሳት መጻሕፍት ማረጋገጫ ነው፡ አያችሁ፡ እግዚአብሔር የተናገረውን የሚያረጋግጥ እስከሆነ ድረስ፡ ያ መልካም ነው። "መንፈስ ቅዱስን ያገኘህበት ምክንያት ይህ ነው፡ በእጅህ ዘይት ስላገኘህ ነው፡" ይላሉ። አሁን፡ እኔ—እኔ በዚያ አልስማም። አያችሁ? አይ፡ ዘይት ከእሱ ጋር የሆነ ግንኙነት አለው ብዬ አላምንም። እና ያ ደም ሊፈውስ እና ሊያድን ከሆነ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ምን ሆነ? ያ ዘይት የሚፈውስ ከሆነ፡ የእርሱ ቁስሉስ? አያችሁ? አያችሁ?

92 መሪው እንዲመጣ እወዳለው፡ ወደ ቃሉ እውነት የሚያመጣችሁ፡ ከዚያ ዜሮ እንደገባችሁ እና ለመቁጠር ዝግጁ መሆናችሁን ታውቃላችሁ። ያ ትክክል ነው፡ ለመብረር በመዘጋጀት። አዎን፡ ዋዳጄ። አዋ ለምን? መሪው እውን የሚያደርገው እሱ ነው።

93 እዚህ የመጽሓፍ ቅዱስ ጥቅስ ይዣለሁ፡ እነዚህን ጥቅሶችን ሰጥቻቸዋለሁ፡ ግን ይህን ማንበብ እፈልጋለሁ። ሁለተኛው ጴጥሮስ ነው፡ 1ኛው ምዕራፍ፡ 21 ኛ ቁጥር።

> **ትን... ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፡ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።**

94 ትንቢቱ እንዴት መጣ? በሰው ፈቃድ፡ በሃይማኖት ተቋማት መግለጫ አይደለም፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ፡ ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ

ሲንቀሳቀሱ። እሱ ሁል ጊዜ የእግዚአብሔር መሪ ነው። ያ በእሳት ዓምድ ውስጥ የነበረው መንፈስ ቅዱስ ነበር፡ ያ መንፈስ ቅዱስ ነበር፡ ክርስቶስ እንደነበረ ማንም ያውቃል። ሙሴ ግብፅን ተወ፡ ስለ ክርስቶስን መነቀፍን ከግብፅ ባለጠግነት የበለጠ ቈጠረ። ክርስቶስ አንዱ ነበር። ደህና፡ እዚያ ቆመው እንደዚህ ሲሉ ጊዜ፡ "ደህና፡ አንተ ነኝ ትላለህ... ለምን፡ ዕድሜህ ከሃምሳ ዓመት በላይ ያልሆነህ፡ እና አብርሃምን አይቻለሁ ትላለህን?"

95 "አብርሃም ከመወለዱ በፊት፡ እኔ ነበርኩ፡" አለ። ሙሴን በእሳት ዓምድ ውስጥ በሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ ያገኘሁት **እኔ ነኝ**። አዎን፡ ዎዳጄ። እርሱ እግዚአብሔር በሥጋ የተገለጠ ነው። ሦስተኛ ሰው አይደለም፡ በተለየ ቢሮ ውስጥ ተመሳሳይ ሰው። ሦስት አማልክት አይደሉም፡ የአንድ አምላክ ሦስት ቢሮዎች። በትክክል።

96 ደህና፡ አሁን፡ ቅዱሳት መጻሕፍት። ሁል ጊዜ፡ እግዚአብሔር ሲሰጥ፡ መልካሙን ይሰጣል። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑን የሚያጠናክርበትን መንገድ ሲያዘጋጅ፡ ያዘጋጀው የተሻለውን ነው። አዳምና ሔዋንን በኤደን ገነት፡ በሰጣቸው ጊዜ፡ የሰጣቸው ቃሉን ነበር። "ከዚህ ቃል ጀርባ ትቆያላችሁ፡ እና እናንተ ደህና ናችሁ። ከዚህ ብትወጡ፡ ግን ከእርሱ በበላችሁ ቀን በዚያ ቀን ትሞታላችሁ።" እግዚአብሔር ዘዴውን ቀይሮ አያውቅም። ሰይጣንም ከቶ አልተለወጠም፡ ወደ አዳምና ሔዋን እንዴት እንደገባ፡ ዛሬም ወደ እነርሱ እንደዚሁ ይገባል። ለምን? ለማስረዳት በመሞከር። "አሁን፡ እግዚአብሔር እንደማይፈቅድ ምክንያት አለው። ኦህ፡ እግዚአብሔር ተናግሯል፡" ሰይጣን "ቅዱስ አምላክ ግን ይህን አያደርግም፡" አለ። በእርግጥ ያደርጋል፡ ምክንያቱም አደርገዋለሁ ስላለ!

97 እና ያ ዛሬ ሰዎች የሚሉት ነገር ነው፡ "ኦህ፡ አሁን ጠብቅ! አሁን አታምኑም፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ብሄድና አሥራቴን ብከፍል፡ እና **ይህን** አደርጋለሁ፡ **ያንንም** አደርጋለው፡ እግዚአብሔር ወደዚያ ሊጥለኝ ነው?" ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንኳን ሊረዳ ኣይችልም! አያችሁ? ምንም ምህረት የለም! "ደህና፡ ምስኪኑ ሽማግሌ፡ ምስኪኗ ድሃ አሮጊት፡ መልካምና ምስኪን ነፍስ አላቸው።" እግዚአብሔርን የሚያዩበት ብቸኛው መንገድ፡ ዳግመኛ በመወለድ ነው። ይኸው ነው። ምን ያህል ትንሽ፡ ስንት አመት፡ ምንም ያህል ልጅ ቢሆኑ፡ ምን እንዳደረጉ፡ ምን ያህል ቤተ ክርስቲያን እንደሄዱ እኔ ግድ አይሰጠኝም፡ ምን ያህል ድርጅቶቹን እንደሚያውቁ፡ ምን ያህል ሃይማኖቶቹን ማንበብ እንደሚችሉ እኔ ግድ አይሰጠኝም። ለመጀመር ዳግመኛ መወለድ አለባችሁ ወይም ሲጀመር፡ በመሠረቱ ላይ እንኳን አይደላችሁም፡ ያ በትክክል ልክ ነው።

98 ስለዚህ፡ አያችሁ፡ መሪ ያስፈልጋቿል። ወደ እውነት ይመራችኋል፡ እውነትም ቃሉ ነው። ይመራቿል። እና ሁልጊዜም ሲመራ ነበር። እግዚአብሔር ምንም ነገር መቀየር የለበትም፡ ምክንያቱም እሱ ማለቂያ የለውም እና የተሻለውን ያውቃል። እርሱ በሁሉም ቦታ የሚገኝ ነው፡ እርሱ ሁሉን አዋቂ ነው፡ እርሱ— እሱ ሁሉም ነገር ነው። ትክክል ነው፡ እግዚአብሔር እንደዛ ነው፡ ስለዚህ መቀየር የለበትም። ደህና።

99 እሱ የሚመራችሁን መንገድ አረጋጋጭ ነው። መንፈስ ቅዱስ፡ መሪ፡ እሱ

የሚያስተምረውን ተመሳሳይ ቃል አረጋጋጭ ነው። አሁን፡ ሉቃስ በመሪው ተመርቷል፡ ማለትም፡ “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፡ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ሰበኩ። ያመነ የተጠመቀም ይድናል፡ ያላመነም ይፈረድበታል። ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡ በሰሜ አጋንንትን ያወጣሉ፡ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፡ እባቦችን ይይዛሉ፡ የሚገድልም ይጠጣሉ፡ እጃቸውንም በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ።” መጽሐፍም እንዲህ ይላል፡ “በየቦታው ወጡ፡” በመሪው ተመሩ፡ ታውቃላችሁ፡ “በብዙ ምልክቶች፡ ቃሉን ሰበኩ።” ምን ነበር? መሪው ያ እውነት እንደነበር ያረጋግጣል!

100 ያ የእግዚአብሔር ፖሊሲ ነበር። በዚህ መንገድ ነው የተቀመጠው። ያ የእሱ ፕሮግራም ነው፡ ከእሱ መለወጥ አይችልም፡ ምክንያቱም እሱ ፍጻሜ የለውም። አሜን። ከእሱ ሊለወጥ አይችልም፡ እሱ አምላክ ነው። እኔ ሰው ነኝ፡ ልለወጥ እችላለሁ። እናንተ ልትለወጡ ትችላላችሁ፡ ወንድ እና ሴት ናችሁ። ነገር ግን እግዚአብሔር ሊለወጥ አይችልም። እኔ ፍጻሜ አለኝ፡ ስህተት መሰራት እና ስህተት መናገር እችላለሁ፡ ሁላችንም እንደምንችለው። እግዚአብሔር ግን ሊለውጥ አይችልም። የእርሱ የመጀመሪያው ውሳኔ ፍጹም ነው። እግዚአብሔር የሚሠራበት መንገድ፡ በእያንዳንዱ ጊዜ ማድረግ ያለበት በዚህ መንገድ ነው። ኃጢአተኛን ለማዳን በቦታው ላይ ከጠራ፡ በአንድ ነገር ላይ ተመሰርቶ ያድነዋል። በሚቀጥለው ጊዜ አንድ ኃጢአተኛ ሲመጣ፡ እሱ ተመሳሳይ እርምጃ መውሰድ አለበት፡ ወይም ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሰራ ስህተት ሠርቷል። አሜን። እወደዋለሁ። እውነት እንደሆነ አውቃለሁ።

101 እኔ የሃምሳ-ሶስት አመቴ ነው፡ እዚህ ለሰላሳ-ሶስት አመት ተኩል ወንጌልን እየሰበኩ፡ እርሱ ሲሳሳት አይቼው አላውቅም። በአለም ላይ ሰባት ጊዜ በዓለም ዙሪያ፡ በሁሉም ኃይማኖቶች እና በሁሉም ነገሮች ሲፈተን አይቼዋለሁ፡ በፊት በአንድ ጊዜ ከግማሽ ሚሊዮን፡ እና በጭራሽ አልወደቀም። ከሆነ መጽሐፍ አልናገርም፡ ከግል ተሞክሮ ነው የምናገረው፡ እግዚአብሔር ከቃሉ ጀርባ ቆሞ እንደሚያከብረው አውቃለሁ። አሁን፡ የሆነ ሃይማኖት ካላችሁ፡ ያንን ብትመለከቱት ይሻላችኋል። መንፈስ ቅዱስ ግን የእግዚአብሔርን ቃል ይደግፋል።

102 በቅዱስ ዮሐንስ፡ ምእራፍ 1 ቍጥር 1 ላይ፡ እርሱ ቃል ነው፡ እርሱ መሪ ነው፡ ብሏል፡ “በመጀመርያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሄር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሄር ነበረ። ቃልም ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ።” ይገርማል!

103 ጴጥሮስ በሐዋርያት ሥራ 2፡38 ላይ፡ መንፈስ ቅዱስን እንዴት እንደሚቀበል፡ ተመርቶ ሲያወራ ነበር፡ እንዲህ አለ፡ “ንስሐ ግቡ፡ እያንዳንዳችሁም፡ ለኃጢአታችሁ ስርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ እና ከዚያ መሪው ከዚያ ይወስዳቿል።” አዎ፡ መደረግ ያለበት ነገር ያ ነው። በመጀመሪያ፡ እነዚህን ነገሮች ስለካዳችሁ ለኃጢአታችሁ፡ ላለማመናችሁ፡ ንስሐ ግቡ። ንሰሓ ግቡ፡ እና ተጠመቁ፡ እና ያኔ መሪው ከዚያ ይወስዳቿል። አያችሁ፡ ያ የእናንተ ግዴታ ነው። ንሳሓ መግባት ግዴታችሁ ነው። መጠመቅ ግዴታችሁ ነው። ከዚያ እናንተን ከዚያ መውሰድ የመሪው ግዴታ ነው፡ ከበጎነት ወደ እውቀት፡ ወደ ራስን መግዛት፡ ወደ ትዕግስት፡ ወደ እግዚአብሔርንም መምሰል፡ እና ወደ ወንድማማች መዋደድ መምራት፡ እናም መንፈስ ቅዱስም ያትማቿል። አያችሁ? እንግዲያውስ እናንተ የእግዚአብሔር ሙሉ ቁመና

ናችሁ፡ እውነተኛ የእግዚአብሔር ወንድ ነህ፡ እውነተኛ የእግዚአብሔር ሴት ነሽ፡ በክርስቶስ መልሕቅ የሆናችሁ ናችሁ። በጣም ደስ ይላል፡ በክርስቶስ መልሕቅ ያስድዳል።

104 አዎን፡ ማርቆስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ነው፡ ማርቆስ 16ን የጻፈው፡ ትክክል ነው።

105 ዮሐንስ ራዕይን ሲጽፍ ተመርቶ ነው። በመሪው ተመሪቶ ነው። እንዲህ ለማለትም በመሪ ተመርቶ ነው፡ "ከእርሱ አንዲት ቃል የቀነሰ፡ ወይም በእርሱ ላይ አንዲት ቃል የጨመረ፡ ከሕይወት መጽሐፍ ውስጥ፡ የእርሱ ድርሻ፡ በተመሳሳይ ይወሰዳል።"

106 አሁን፡ አንድን ነገር በእግዚአብሔር ቃል እንዴት ትተካላችሁ፡ እና አሁንም በመንፈስ ቅዱስ እንመራለን ትላላችሁ? ትርጉም አልባ፡ አይደል? አይ፡ ዎዳጄ። አይደለም።

107 እሱ የሕይወት መሪዬ ነበር። ወደ ሕይወትም መርቶኛል። ወደ ሕይወት የመራኝ እርሱ ነው፡ እርሱም ሕይወቴ ነው። ያለ እሱ ሕይወት የለኝም። ያለ እሱ ሌላ ምንም አልፈልግም። እሱ ለእኔ ሁሉ-በ-ሁሉ ነው። በመከራዬ ሰዓት፡ ከጎኔ ይቆማል። ትላንት ባርኮኛል፡ ዛሬም እንዲሁ አድርገዋል። ምን መጠበቅ እችላለሁ? ለዘላለም ያው ነው፡ ስሙን ባርኩት! አሜን። አዎን፡ ዎዳጄ። ቃል ገብቷል። እሱ ያደርገዋል። እሱ ሕይወቴ ነው፡ እርሱ መሪዬ ነው፡ ሁሉ-በ-ሁሉ ነው። በእርሱ ታምኛለሁ። አንዳንድ ከባድ ፈተናዎች አጋጥመውኛል። በሄድኩበት ሁሉ እምነዋለው። እንደዛ እንድታደርጉት እፈልጋለሁ። ለመታጠብ ከሄዳችሁ፡ እናንተ ሴቶች፡ እመኑት። መሀል ከተማ ከሄዳችሁ፡ እመኑት።

108 የሆነ ጊዜ ኃይለኛ የጫካ ሰው ነኝ ብዬ ያሰብኩበት ወቅት ነበር፡ ታውቃላችሁ፡ በጣም አድን ነበርና። በአሳቤ፡ "ማንም የማያታልለው፡ በፍጹም የማይሳሳት... ልታስጠፉኝ የማትችሉ። እናቴ ግማሽ ህንዳዊ ነበረች፡ እና ያንን ደስ ይለኛል። ኦህ፡ ይገርማል! በጫካ ውስጥ ልታስጠፉኝ አትችሉም፡ የት እንዳለሁ አውቃለሁ።"

109 እና በጫጉላዮ ላይ፡ ሚስቴን ትንሽ አታልዬ፡ እንዲህ አልኳት፡ "ታውቅያለሽ ማር፡ በጥቅምት ሃያ-ሶስት ብንጋባ፡ ጥሩ ይሆንልናል።" እርግጥ ነው፡ ጌታ እንዳደርግ የነገረኝ ያኔ ነው።

110 እና እንዲህ አሰብኩ፡ "አሁን፡ ለትንሽ ለጫጉላ ሽርሽር፡ ገንዘቤን አጠራቅሜ፡ እና በኒያጋራ ፏፏቴ እወስዳታለሁ፡ እና በ አዲሮንዳክ ላይ እሄድና ትንሽ አደን አድናለው።" አያችሁ? እናም እሷን እና ቢሊ ወሰድኳቸው፡ እሱ ትንሽ ምጢጥዬ ነገር ነበር። እና ስለዚህ እሷን በጫጉላ ሽርሽር ላይ መውሰድ ነበረብኝ፡ እና በአደን ጉዞም፡ ጭምር ነበር፡ ታውቃላችሁ። ስለዚህ—ስለዚህ ያ ማድረግ ጥሩ ነገር ነው ብዬ አሰብኩ። እና ስለዚህ እሷን ወሰድኳት፡ እና...

111 ለደን ጠባቂው፡ ሚስተር ዴንተን ጻፍኩ። እና ወደ ሃሪከን ተራራ እየወጣን ነበር። እኔም አልኩት፡ "ሚስተር ዴንተን፡ እየመጣሁ ነው፡ በዚህ በልግ ከአንተ ጋር ድብ ማደን እፈልጋለሁ።"

112 እርሱም "እሺ ቢሊ ና፡" አለኝ። ስለዚህም "**በዚህ-በዚያ** ቀን እዛ እገኛለሁ፡" አለኝ። ደህና፡ እኔና ባለቤቴ እና ቢሊ፡ አንድ ቀን ቀደም ብለን

እዚያ ደረስን፡ እና ጎጆው ዝግ ነበር። ጫካው ላይ እንደ መደገፍ ትንሽ ዛመም-ብሎ ነበር።

113 ቦታው፡ እኔና ወንድም ፍሬድ ሶትማን በቅርብ እዚያ ሄደን ረግጠነው ነበር። በዚያም መንፈስ ቅዱስ፡ እዚያ ቆሞ፡ ያ ቢጫ ብርሃን በጫካ ውስጥ ሲዘዋወር እየሁት፡ እና ፍሬድ እዚያ ቆሞ ነበር። "አንተን ላናግርህ እፈልጋለሁና፡ ነገ፡ ለብቻህ ና፡" አለኝ። "ወጥመድ አዘጋጅተውብሃልና፡ ተጠንቀቅ፡" አለኝ። አለኝም፡ "ንቁ ሁን!" ልክ ነው ወንድም ፍሬድ? እናም ሄጄ በዚያ ምሽት በመቶ ለሚቆጠሩ ሰዎች ነገርኳቸው፡ በቬርሞንት፡ እንደዝህ አልኳቼው፡ "ለእኔ የተዘጋጄ አንድ ወጥመድ አለ፣ እሱን ላየው ነው። የት እንዳለ አላውቅም።" እና በሚቀጥለው ምሽት፡ ኤሃው መጣ፡ እዚያ ነበር። "እዚህ ነው የተዘጋጀው ወጥመድ ያለው።" አለኝ፡ አዎን፡ ዋዳጄ። መንፈስ ቅዱስ ግን ምን እንዳደርግ መራኝ። እና፡ ኦህ፡ ይገርማል፡ ያም ልክ ነበር! ኦህ፡ ብዙዎቻችሁ ምን እንደነበረ ታውቃላችሁ። ለመናገር ጊዜ የለኝም።

114 ነገር ግን በዚያን ጊዜ በዚያ ቦታ ላይ ቆሞ፡ ልክ በዚያ ቀን ቅዝቃዜው ይጀምራል። በማግስቱ ሚስተር ዴንተን እየመጣ ነበር፡ እንዲህ አልኳት፡ "ታውቂያለሽ፡ ማር፡ ወደ ቤት ለመውሰድ ትልቅ—ብዙ ገንዘብ ባገኝ ጥሩ ነበር።" "ሄድን... እነዚህን ሳንቲሞች ማጠራቀም ነበረብኝ፡ እና ገና አዲስ ተጋቢዎች ነበርን።" እኔም፡ "ዛሬ ትንሽ ማደን ከቻልኩ የክረምታችንን ስጋ እናገኛለን" አልኳት።

115 እርሰዋም፡ "መልካም፡ ቀጥል ሂድ፡ ቢሊ።" አለችኝ፡ "አሁን፡ ታስታውሳለህ፡ በእነዚህ ጫካዎች ውስጥ በጭራሽ አልነበርኩም፡" አለችኝ። እሷ በተራሮች ላይ ሀያ-አምስት ማይል ርቀት ላይ ነበረች፡ ታውቃላችሁ፡ እና እንዲህ አለች፡ "ስለዚህ ጉዳይ ምንም አላውቅም።" እርሰዋም፡ "ስለዚህ እኔ... "

116 እኔም፡ "መልካም፡ አሁን፡ ታስታውሺያለሽ፡ ከሁለት አመት በፊት ነበር እነዚያን ሶስት ድብ የገደልኳቸው። ያ እዚያ ካለው ከተራራው ጫፍ በስተጀርባ በኩል ነበር" አልኳት። እኔም አልኳት፡ "አሁን፡ ብዙ ገንዘብ አገኛለሁ እና ትንሽ ድብ እናገኛለን፡" እኔም አልኳት፡ "የክረምቱን ስጋ እናስገባለን።" መልካም፡ ያ በጣም ጥሩ ይመስላል፡ ታውቃላችሁ። (እና ጥቁር እንጆሪዎችን መረጥን፡ እና የድንጋይ ከሰል አገኘን—ለዚያ ክረምት፣ እና ከዚያም ቢሊ ሸጣቸው፡ እና እኔ እና ሚዳ ከፓትሮሌ ከወረድኩ በኋላ አንድ ምሽት ወሰድናቸው።) ስለዚህ እኔ—እኔ እንደዚህ አልኩ፡ "ደህና፡ ጠመንጃዬን ይዤ፡ ወደዚህ እወርዳለሁ።" "እዚህ ውስጥ ብዙ አጋዘን አለ፡ አንዱን አገኛለሁ፡" አልኩ። እና "ታውቂያለሽ፡" አልኳት፡ "ሄጄ አገኛለሁ፡" አልኳት። "ያኔ... እኔም ከትንሽ ጊዜ በኋላ እመለሳለሁ፡" አልኳት።

አሷም፡ "እሺ" አለች።

117 ስለዚህ፡ ሰጀምር፡ በጣም አነስተኛ ነበር። እና ማንኛችሁም የኒው ሃምስፌር ሰዎች፡ እና እዚያ በኒው ኢንግላንድ ውስጥ ያላችሁ፡ ያ ጭጋግ ሲወርድ ምን ማለቴ እንደሆነ ታውቃላችሁ፡ ወይም በተራሮች ላይ ችየትም ሆናችሁ፡ የት እንዳላችሁ አታውቁም። ይኼው ነው በቃ። ከእናንተ በፊት እጃችሁን ማየት አትችሉም፡. ስለዚህ እኔ ወደ ታች በአንድ በኩል ትንሽ—

ትንሽ እንዲህ፡ እያቆራረጥኩ ጀመርኩ፡ እንደ መውረድ ነገር፡ ሽንተረሩን አልፎ ወጣው። እና ፓንተር እንዳለ አሰተዋልኩ፡ እዚህ የአገሪቱ ክፍል እንዲህ ትጠሩታላችሁ። በምዕራብ በኩል፡ አነር፡ ብለን እንጠራዋለን። እዚያ ላይ፡ የተራራ አንበሳ፡ ብለው ይጠሩታል። ሁለቱም አንድ አይነት እንሰሳ ናቼው። እሱ በእውነቱ፡ የድመት ዝርያ ነው። ተመሳሳይ ድመት፡ ወደ ዘጠኝ ጫማ ይረዝማል፡ ወደ አንድ መቶ ሃምሳ፡ ሁለት መቶ ፓውንድ ይመዝናል። እሱ መንገዱን አቋረጠ፡ እና ሽጉጡን በፍጥነት አንሽራተትኩ፡ እሱን ለመተኮስ በቂ ፍጥነት አልነበረኝም።

118 መልካም፡ ይህን አነር እያሳደድኩ፡ የተንቀሳቀሰበትን ቅጠሎችን እየተመለከትኩ፡ ኮረብታው ላይ፡ ተንሸራትቼ ወጣሁ። እሱን መሰማት እችል ነበር። አራት እግር ነበረው። ባለ-ሁለት እግር እንስሳ እንዳልሆነ አውቅ ነበር፡ አራት እግር አለው። እና ሚዳቆ እንዳልሆነ አውቄ ነበር፡ ምክንያቱም ሚዳቆ ይረግጣል። ታውቃላችሁ፡ እንዴ፡ ድመት፡ እሱም በእውነቱ በቀላሉ ይንሸራተታል። ድብ ሲራመድ እግሩን ያንከባልላል። እና አነር መሆን እንዳለበት አወቅሁ። እና እሱ ከእንጨት ጀርባ ነበር እና አላየውትም ነበር፡ ላየው ሰል፡ ጠፋብኝ።

119 እና ቅጠሎቹን በሚንቀሳቀሰበት ቦታ ተመለከትኩ፡ ታውቃላችሁ፡ ከተራራው አናት ላይ፡ ታውቃላችሁ፡ እንደዚህ ወደ ታች፡ ያ ሁሉ ደመና፡ ጭጋግ ሲወርድ አልታየኝም ነበር። ተንሸራትቼ፡ በታላቅ ሽለቆ ውስጥ ወረድኩ፡ እና ይህን አነር ተከትዬ ወደ ጃያንትስ ወጣሁ። “ከጥቂት ጊዜ በኋላ እይዘዋለሁ፡” በማለት አሰብኩ። አንድ ቦታ አየሁ፡ እናም ከፍ ባለ ቦታ ላይ ሮጥኩ፡ እና እንደዛ ዙሪያውን እመለከት ነበር፡ እና ዙሪያውን አየሁት፡ እሱን ማየት እችል እንደሆነ አየሁ፡ በትክክል በቅርበት አዳመጥኩ፡ እና ውረድኩ፡ እንደገና ተንሸራተትኩ። በዝግታ እየረገጠ፡ ከፊቴ ሲሄድ፡ ልትሰሙት ትችላላችሁ። አያችሁ፡ እርሱ ዛፎቹን እየመታ ሰለነበር እሱን መከተል አልቻልኩም። አያችሁ፡ ብልህ ሆነ፡ በዛፎች ላይ ወጥቶ ከዛፍ ወደ ዛፍ እየዘለለ ነበር። ከዚያ እሱን እዚያ ልከተለው እንደማልችል አወቀ። ኦህ፡ ያሰብኩት፡ “ኦህ፡ ለማንኛውም!”

120 እናም ወደ ተራሮች መመለሰ ጀመርኩ፡ እና አንድ ድብ፡ አንድ ወንድ ድብ እንዳለ አሸተትኩ። “በቃ፡ አሁን አገኘዋለው፡ ጥሩ ነው!” ብዬ አሰብኩ፡ እንደገና አሸተትኩ፡ እና ትንሽ ወደ ፊት ሄድኩ፡ እና ሁሉንም አይነት ምልክቶች እና ሁሉንም ነገር ተመለከትኩ። አንድ ነገር ማየት አልቻልኩም፡ ወደ ኋላ ተመለሰና፡ ከተራራው ማዶ ወረደ። እና ከዚያ ትንሽ ጭጋጋማ እየሆነብኝ እንደሆነ፡ ማሰተዋል ጀመርኩ። እና እንደገና አሸተትኩ፡ አየሩ ላይ በሆነ ቦታ ነበር። እንዲህ አልኩ፡ “አይ። አሁን፡ ምን ሆነ፡ ነፋሱ **በዚህ** መንገድ እየመጣ ነበር፡ እናም መጣሁ... የድብ ሽታ **ከዚህ** ወደ ታች ይወርድ ነበር፡ እና አሁን ተሻግሬያለሁ እና ነፋሱ ከዚህ በሌላ አቅጣጫ እየመጣ ነው። ሰለዚህ ድቡን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደሸተትኩበት መመለስ አለብኝ፡ እና ከዚያ እወስደዋለው” አልኩ።

121 እና በመመለስ መንገዴ፡ ካንየን አሻግረው ተመለከትኩ፡ ቁጥቋጦዋቹ ሲንቀሳቀሱ አየሁ። እና እንደዛ ሳደርግ፡ አንድ ጥቁር ነገር ተንቀሳቀሰ። “እሱ እዝሁ አለ በቃ፡” ብዬ አሰብኩ። እኔ በጠመንጃው ውስጥ አንድ ጥይት ወረወርኩ፡ በእውነቱ በፍጥነት፡ ቆምኩ። እና፡ ሲሆን፡ ትልቅ ብዙ ገንዘብ ነበር፡

ትልቅ ብዙ ነበር። ያሰብኩት፡ “ለማንኛውም፡ እኔም የምፈልገው ያንን ነው።” በጥይቱ ተኮስኩት።

122 ያሰብኩት፡ “መልካም!” እንደዛ ዓይነት መሆኑን በጭራሽ አላስተዋልኩም... እኔ እሱን ለማስተካከል ጊዜ ነበር፡ አየሁ... እጆቼን አጽድቼ ቢላዬን አስተካክዬ፡ መለስኩት። እኔም አሰብኩ፡ “እግዚአብሄርን ይመስገን! አመሰግንሀለሁ፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ የክረምቱን ስጋ ሰጠኸኝ። እግዚአብሔር ይመስገን!” እና ጠመንጃዬን አነሣሁ። ያሰብኩት፡ “አሁን ወደ ካንየን ወደላይ እመለሳለሁ።” እንዲህ አልኩ፡ “ወደዚህ ተመልከት፡ ጃል፡ ማዕበል እየመጣ ነው። ከዚህ ወጥቼ ወደነ ሚዳ እና ወደ ሌሎቹ ብመለስ ይሻለኛል።” እንዲህ ኣልኩ፡ “መፍጠን አለብኝ።”

123 የሄድኩበት ተራራ ላይ፡ ትልቁን ቀይ ኮቴን ከፈትኩ፡ እናም ተራራውን **እንደዚህ** እየሮጥኩ ነበር የወጣሁት፡ ዙሪያን። መጀመሪያ የምታውቁት ነገር፡ ያሰብኩት፡ “ይገርማል፡ የት ነው ያጠፋሁት? ” ነፋሱ አሰቀድሞ ወድቆ ነበር፡ ዛፎቹ አንዱ በአንዱ ላይ ይወድቁ ነበር። ያሰብኩት፡ “የት ነው ያጠፋሁት? ” ዞርኩኝ። እኔ—በቀጥታ ወደ ሃሪከን ተራራ እንደምሄድ አውቄ ነበር። ግን በአጋጣሚ ቆምኩኝ፡ እያለብኩ ነበር፡ እንዲህ አሰብኩ፡ “እዚህ ያለው ችግር ምንድነው? ግማሽ ሰዓት፡ ወይም ሶስት ሩብ ሄጃለሁ፡ እና ትቼ የሄድኩበትን ቦታ አላገኘሁትም።” ቀና ብዬ አየሁ፡ እዛ ሚዳቆዬን ሰቀልኩት። ዞሬ ዞሬ ልክ በተመሳሳይ ቦታ ነበርኩ። “እንዴ፡ ምንድነው አደረግሁት፡” አልኩኝ?

124 መልካም፡ እንደገና ተነሳሁ። እንዲህ አሰብኩ፡ “አሁንማ አደርገዋለሁ፡ አላስተዋልኩም ነበርና።” እያንዳንዷን እንቅስቃሴ በየቦታው አየሁ፡ ተመለከትኩ። መፈለጌን፡ መፈለጌን፡ መፈለጌን ቀጠልኩ። ደመናዎች እየመጡ ነው፡ የበረዶ አውሎ ንፋስ በመንገድ ላይ እንደነበረ አውቃለሁ፡ ጭጋግ ዝቅ ብሎ ተንጠልጥሏል፡ እና ከዚያ ማስተዋል ጀመርኩ። እንዲህ አሰብኩ፡ “ትንሽ ወደ ፊት እሄዳለሁ፡” ቀጠልኩ፡ ቀጠልኩ፡ ቀጠልኩ፡ ቀጠልኩ፡ ቀጠልኩ፡ ቀጠልኩ፡ ቀጠልኩ። እኔም አሰብኩ፡ “እንዴ፡ እንግዳ ነገር ነው፡ ይህንን ቦታ ከዚህ በፊት ያየሁት ይመስላል።” እኔም ተመለከትኩኝ፡ በዚያም ሚዳቆዬን ሰቀልኩ። አያችሁ?

125 ምን ላይ እንደነበርኩ ታውቃላችሁ? ህንዶች እንዲህ ይሉታል “የሞት ጎዳና።” አያችሁ፡ በክብ፡ ዙሪያ ዙሪያውን እየተራመዳችሁ ነው። እንደው፡ ስለራሴ በፍጹም ሊጠፋ የማይችል ጥሩ መሪ ነኝ ብዬ አስብ ነበር። አያችሁ፡ በጫካ ውስጥ የሚነግረኝ አያስፈልገኝም ነበር፡ መንገዴን አውቀው ነበር። አያችሁ?

126 እና እንደገና ጀመርኩ። እንዲህ አልኩ፡ “ይህን መሳሳት አልችልም።” እና እንደገና ተመልሼ መጣሁ።

127 ትንሽ ወደ ተራራው ወደ ላይ ወጣው፡ ከዚያ ንፋሱ መንፈስ ጀመረ። ኦህ፡ ይገርማል፡ በረዶ በሁሉም ቦታ! ወደ ጨለማ ማለት ይቻላል። እና ሚዳ በዚያ ምሽት በምድረ በዳ እንደምትሞት አውቄ ነበር፡ እራሷን እንዴት መንከባከብ እንዳለባት አታውቅም። እና ቢሊ ገና የአራት አመት፡ ሶስት አመት ልጅ ነበር፡ ትንሽዬ ምጥጥዬ ነገር። እናም እንዲህ አሰብኩ፡ “አሁን ምን ያደርጉ ይሆን? ” መልካም፡ እስከዚህ ድረስ መጣሁ እና ትንሽ ለጥ ያለ ሳር ነካሁ፡ እንዲህ

አሰብኩ፡ “የሆነ ሜዳ መሬት ውስጥ ነኝ፡ እና ምንም ነገር አይታየኝም፡ ሁሉም ጭጋጋማ ነው።” አሁን እየዞርኩ ነበር።

128 እንደተለመደው፡ ከእኔ ጋር የሆነ ሰው ቢኖረኝ፡ ቦታ አግኝቼ እይዝ ነበር። አውሎ ነፋሱ እስኪያልቅ ድረስ አንድ፡ ወይም ሁለት ቀን እስኪያልቅ ድረስ እጠብቅ ነበር፡ ከዚያም እወጣ ነበር። የአጋዘነን ቆራሪጩ... ከኋላዬ አይ አረገውና፡ ገብቼ፡ እበላና፡ ስለ እርሱ እረሳለው። ነገር ግን ያንን ማድረግ አትችሉም፡ እና ሚስታችሁ እና ልጆችሁ እዚያ ጫካ ውስጥ ተኝተው፡ እየጠፉ ነው፡ አያችሁ?

129 ስለዚህ ማሰብ ጀመርኩ፡ “ምን ላደርግ እችላለው? ” ስለዚህ ትንሽ ሪቂ መጣው። እኔም አሰብኩ፡ “ቆይ፡ እስኪ። የመጀመሪያውን ሸለቆን ስሻገር፡ ነፋሱ ፊቴ ለፊቴ ነበር፡ በዚህ መንገድ ሳልመጣ አልቀርም። በዚህ መንገድ መጥቼ መሆን አለበት።” የት እንደነበርኩ ማወቅ አልቻልኩም እንጂ፡ ታች እስከ ጃይንቶቹ አካባቢ ተቅበዝብዤ ነበር። “ኦህ!” አልኩ፡ መጨነቅ ጀመርኩ። እኔም አሰብኩ፡ “ቢሊ፡ አንድ ደቂቃ ቆይ፡ አልጠፋህም፡” ራሴን ለማታለል እየሞከርኩ ነው። ማታለል አይቻልም። አይ፡ አይ። ውስጣዊ ህሊናችሁ እንደተሳሳታችሁ ይነግራቿል።

130 ኦህ፡ እናንተ—እንደዚህ “ኦህ፡ ቤተ ክርስቲያን ሄያጅ ነኝና፡ ድኛለሁ፡” ለማለት ትሞክራላችሁ። አትጨነቁ፡ ያ የሞት አልጋ እስኪመጣ ድረስ ጠብቁ፡ እና የተለየ እንደሆነ ያኔ ታውቃላችሁ። ሕሊናችሁ ይነግራቿል። በውስጣችሁ የሆነ ነገር እንደተሳሳታችሁ ይነግራቿል። አያችሁ? ብትሞት ቅዱስ አምላክን ማግኘት እንደማትችል ታውቃለህ። ትናንት ማታ እንዳየነው፡ ቅዱሳን መላእክት እንኳን በፊቱ ለመቆም ፊታቸውን መሸፈን አለባቸው። የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ሳይጋርዳችሁ እንዴት ልትቆሙ ነው?

131 አሰብኩ፡ “ኦህ፡ አደርገዋለሁ።” ጀመርኩ። እና የሆነ ነገር እንደሰማሁ ተረዳሁ። ከዚያም ተጨነኩኝ። እኔም አሰብኩ፡ “አሁን፡ ያንን ካደረግኩ፡ እዚሁ ደቅቄ እጠፋለሁ።” ብዙውን ጊዜ የጠፋ ሰው የሚሆነው ያ ነው፡ በጫካ ውስጥ ደቆ ይበሰብሳል። ሽጉጡን ወስዶ፡ እራሱን ያጠፋል፡ ወይም በጉድጓዱ ላይ ወድቆ እግሩ ይሰበራል፡ እና በዚያ ወድቆ፡ እዚያው ይሞታል። ስለዚህ አሰብኩ፡ “ምን ላድርግ? ” ስለዚህ መሄድ ጀመርኩ።

132 እናም አንድ ነገር ደጋግሜ መሰማቴን ቀጠልኩ፡ “ባገኘህ በታላቅ መከራ ረዳትህ ነኝ።” ዝም ብዬ መንገዴን ቀጠልኩ።

133 “አሁን፡ አሁን ትንሽ እየጠፋሁ እንደሆነ ገባኝ፡ የሚናገረኝን ድምፅ እየሰማሁ ነው፡” ብዬ አሰብኩ። መንገዴን ቀጠልኩ። ሄድኩ “**ዊው፡ ዊው፡ ዊው፡**” ታውቃላችሁ፡ ያፏጫል። አሰብኩ፡ “አሁን፡ አልጠፋሁም። የት እንዳለህ ታውቃለህ አይደል፡ ጃል! ምንድነው ችግርህ? ልትጠፋ አትችልም። አንተ—አንተ በጣም ጎበዝ አዳኝ ነህ፡ ልትጠፋ አትችልም።” የራስ-መኩራራት፡ ታውቃላችሁ፡ እራሴን በራሴ እያታለልኩ ነበር።

134 ማታለል አትችሉም። **በዚህ** በታች በኩል የሚሽከረከር መንኮራኩር አለ፡ “ጠፍተሃል እና እንደጠፋክ ታውቃለህ፡ ጃል። አየህ፡ ጠፍተሃል፡” አልኩ።

135 መንቀሳቅሴን ቀጠልኩ፡ “ኦህ፡ አልጠፋሁም! ደህና እሆናለሁ። መውጫ መንገዴን አገኛለሁ።” ነገሮች አስቂኝ መምሰል ጀመሩ፡ ነፋሱ እየተቃረበ ነው።

በረዶ በአየር ላይ መንቀሳቀስ ጀምሯል፡ ትንሹ ሆሚንይ በረዶ፡ “ካፊያ” እንለዋለን። አሰብኩት፡ “ሚስቴ እና ልጄ! እኔ አይሆንም... ” አሰብኩት፡ “ኦህ፡ ይገርማል!”

136 ደግሜ በቀጥታ፡ “ባገኘህ በታላቅ መከራ ረዳትህ ነኝ።” ሲለኝ እንደገና ሰማሁት። በዚያን ጊዜም የወንጌል አገልጋይ ነበርኩ፡ እዚያው በተብርናክሉ ውስጥ ሰባኪ ነበርኩ።

137 ስለዚህ አሰብኩት፡ “ደህና፡ ምን ማድረግ እችላለሁ? ” ቆምኩኝ፡ ሁሉንም ቦታ ተመለከትኩ፡ እና አሁን ጭጋግ ቀድሞኝ ወረደ። እኔ... ያ ነበር። ያኔ ምንም ማድረግ አልተቻለም። አሰብኩ፡ “ኦህ፡ ምን ማድረግ እችላለው? ” እንዲህ አሰብኩ፡ “ዋዳጄ፡ ለመኖር ብቁ አይደለሁም፡ የራስ-መተማመን ስሜት ነበረኝ። አዳኝ ነኝ ብዬ አስብ ነበር፡ ግን አይደለሁም።”

138 ወንድሜ ሆይ፡ በመተኮስ፡ ሁልጊዜም አምነዋለሁ። ሪከርድ አስመዝግቤአለሁ። እና ዓሣ በማጥመድ፡ እኔ ችሎታ የለኝም፡ እሱን ግን ሁልጊዜ አምነዋለሁ። በመተኮስ፡ ደካማ ተኳሽ ነኝ፡ በእሱ ግን የአለም ሪከርዶችን እንድሰብር ፈቀደልኝ። አያችሁ? አጋዘን ስተኩስ፡ ሰባት፡ ሰምንት መቶ ያርድ ርቀት ላይ ነው። ጠመንጃየን አነሰቼ ሰላሳ-አምስቱንም ጭንቅላታቸውን ምንም ሳያመልጠኝ ተኮሼ መታኋቸው። ከቻላችሁ፡ ያንን በየትኛውም ቦታ አንብቡ። አያችሁ? እኔ አይደለሁም፡ እሱ ነው። በእርሱ ታምኛለሁ።

በዚያ ሆኜ ግን፡ እንዲህ አሰብኩ፡ “ምን ላድርግ? ምን ላድርግ? ”

139 ቀጠልኩ... ያ እየተቃረበ፡ እየተቃረበ መጣ፡ “ባገኘህ በታላቅ መከራ ረዳትህ ነኝ፡ ረዳትህ ነኝ።”

140 “የሚያናግረኝ እግዚአብሔር ነውን፡” ብዬ አሰብኩ? ኮፍያዬን አወለቅኩ። የፓትሮል ኮፍያዬን፡ ቀይ መሀረብ ተጠቅልሎበት ነበር። አስቀመጥኩት። ኮቴን አውልቄ፡ እርጥብ ነበር። እና ኮቴን አስቀምጬ፡ ጠመንጃዬን ከዛፉ ዘንድ አስደገፍኩት። እንዲህ አልኩ፡ “የሰማይ አባት ሆይ፡ አሁን ከራሴ በላይ እየሆነብኝ ነው፡ የሚናገረኝን ድምፅ እየሰማሁ ነው። ጌታ ሆይ አንተ ነህን? ” እንዲህ አልኩ፡ “ጌታ ሆይ፡ አዳኝ እንዳልሆንኩ እነግርሃለሁ። እኔ አይደለሁም፡ እኔ—መንገዴን ማግኘት አልቻልኩም። ልትረዳኝ ይገባል። ለመኖር ብቁ አይደለሁም፡ እና ያደረኳቸውን ነገሮች መልሼ እያደረግኩ ነው፡ እዚህ መጥቼ ስለ መጥፋት በጣም አውቃለው። ታስፈልገኛለህ፡ ጌታ ሆይ። ባለቤቴ ጥሩ ሴት ነች። ልጄ፡ ትንሹ ልጄ፡ እናቱ ሞታለች፡ እና ለእሱ እናት ልትሆን እየሞከረች ነው፡ እና አገባኋት። እነሆ እሷም፡ አንድ ልጅም፡ በጫካ ውስጥ ናቸው፡ ሁለቱም ዛሬ ማታ ይሞታሉ። ብርዱ፡ ከዜሮ በታች አስር ይወርዳል፡ እና እንዴት መኖር እንዳለባቸው አያውቁም። ዛሬ ማታ ይሞታሉ። እንዲሞቱ አትተዋቸው፡ እግዚአብሔር። አለመሞታቸውን እንዳይ፡ ወደ እነርሱ ውሰደኝ። እኔ ጠፍቻለው! ጠፋሁ፡ አምላኬ! እኔ—መንገዴን ማግኘት አልቻልኩም። እባክህን አትረዳኝምን? እና ስለ ራስ-ወዳድነቴ ይቅርታ አድርግልኝ! ያለ አንተ ምንም ማድረግ አልችልም፡ አንተ መሪዬ ነህ። እርዳኝ፡ ጌታ ሆይ።”

141 ተነሳሁና፡ “አሜን፡” አልኩ። መሀረቤን አነሳሁ፣ ኮቴን፡ አነሳው፣ ባርኔጣዬን መልሼ አደረኩ፡ ጠመንጃዬን አነሳሁ። እንደዚህ አልኩ፡ “አሁን እኔ እንዴት

መሄድ እንዳለብኝ በቻልኩት መንገድ እራሴን አስተካክዬ፡ በተቻለኝ ሁሉ፡ እና በቀጥታ በአንድ መንገድ እሄዳለሁ፡ ምክንያቱም የት እንደሆነ ባላውቅም፡ በሆነ ቦታ በክብ ውስጥ እየዞርኩ ነው። እኔ ግን ጌታ እግዚአብሔር፡ መሪዬ ሆይ፡ በነገርከኝ መንገድ እሄዳለሁ።"

142 **በዚህ** መንገድ መሄድ ጀመርኩ። እንዲህ አልኩ፡ "ይህ ነው መንገዱ፡ እና ራሴን ማሳመን አለብኝ። **በዚህ** መንገድ እየሄድኩ ነው። በቀጥታ **በዚህ** መንገድ እሄዳለሁ። እኔ አልቀይርም፡ **በዚህ** መንገድ እሄዳለሁ። ትክክል እንደሆንኩ አውቃለሁ። **በዚህ** መንገድ እሄዳለሁ።" በዚያ መንገድ ብሄድ ኖሮ፡ ወደ ካናዳ ልሄድ ነበር። አያችሁ?

143 ልክ ትከሻዬ ላይ የሆነ ነገር ሲነካኝ ተሰማኝ፡ እጅ ነው፡ የሰው እጅ ይመስላል፡ እና፡ በፍጥነት ለማየት ዞወር አልኩ። የቆመ ማንም አልነበረም። "ምንድን ነው? " ብዬ አሰብኩ፡ እነሆ መጽሐፍ ቅዱስ በፊቴ ተቀምጧል። መሪዬ እና ዳኛዬ፡ እግዚአብሔር፡ እዚህ ቆሟል። ቀና ብዬ አየሁት። እና ልክ **በዚህ** መንገድ፡ በሃሪከን ተራራ ላይ ያለውን ግንብ እስከማየው ድረስ ያ ጭጋግ ተጠርጓል። ከእሱ በተቃራኒው መንገድ መሄድ፡ ምርጡ በማደን ችሎታዬ፡ ከእሱ ሪቄ እየሄድኩ ነበር፡ ከዚያ በትክክል ማታ እንደመሆን መሸ። ወዲያው ዞርኩ፡ **እንደዚህ** እራሴን እየመራሁ ዞርኩ። ኮፍያዬን ይዤ እጆቼን ወደላይ አነሳሁና፡ እንዲህ አልኩ፡ "ምራኝ፡ አምላኬ፡ አንተ መሪዬ ነህ።"

144 ጀመርኩ። እኔ በቀጥታ ወደ ብላፍስ መሄድ ነበረብኝ እና ሁሉም ነገር ወደዚያ የሚደርሰው፡ በኋላ እና በኋላ ነው። ከዚያም ጨለመ። አጋዘኖቹ ከፊት ለፊቴ እየዘለሉ ነበር፡ እና ሁሉም ነገር። በአንድ መንገድ ከመጓዝ በስተቀር ምንም ማሰብ አልቻልኩም፡ እስከ ተራራው ራስ ላይ።

145 እና ታወሩ ድረስ መሄድ ከቻልኩ፡ ሚስተር ዴንተን እና እኔ... እኔ በጸደይ ወቅት የሰልክ ሽቦ ዝርጋታ ለመዘርጋት በዚያ እረዳው ነበርና። ከሃሪኬን ተራራ ጀምረን እስከ ሶስት ተኩል ወይም አራት ማይል ድረስ፡ ያለውን የሰልክ ሽቦ የዘረጋነው እና ነን፡ እስከ ታች ካምፕ ድረስ። እና በትክክል በጠባቡ መንገድ ወደ ታች ይወርዳል፡ ነገር ግን፡ እዚያ ላይ በረዶ ሲላለ፡ መንገዱን መለየት አትችሉም። አያችሁ? እና ለመሄድ፡ ነፋሱ እየነፈሰ ነው ሁሉም ነገር፡ ጨለማ እና አውሎ ንፋስ ነበር እና፡ የት እንዳላችሁ ማወቅ አትችሉም። መልካም፡ ከጨለመ በኋላ፡ ማድረግ የምችለው ብቸኛው ነገር፡ እኔ አላውቅም ነበር... በአንድ መንገድ ልክ ወደ ተራራው፡ እንደሚሄድ አውቃለሁ። ወደ ተራራ መውጣት ስላለብኝ፡ ግንቡ ከተራራው ጫፍ ላይ ተቀምጧል፡ እና ወደ እሱ ለመድረስ ስድስት ማይል ያህል ነበረኝ። እስቲ አስቡት፡ በአንድ ቀዳዳ ብቻ፡ ስድስት ማይሎችን፡ ያ ጭጋግ ወደ ኋላ እየጸዳ፡ እስከማየው ድረስ!

146 እና ከዚያ እኔ—ጠመንጃዬን **በዚህ** እጄ ላይ አንጠንጥዬ፡ እና **ይህን** እጄን ወደ ላይ አነሳሁ፡ ምክንያቱም የሰልክ ገመድ ወደ ጎጆ፡ ወደ ታች እየሄደ ያለውን ገመድ የቀጠልኩት እኔ ነበርኩ፡ ከሚስቴ ጋር ሊያወራ ይችል ዘንድ፡ ከዚያ ከተራራው፡ መደወል እንዲችል ነው። እና በዚያ በጸደይ ወራት ቁልቁል እንዲያወርድ ልረዳው ነበር። እኔም **እንዲህ** ብዬ፡ እጄን አነሳሁ፡ "ኦ አምላኬ ሆይ፡ ያንን ሽቦ እንድነካ ፍቀድልኝ።" በመራመድ፡ ክንዴ በጣም ህመም ተሰማው፡ ደክሞኛል፡ በደምብ ልይዘው አልቻልኩም፡ እና ዝቅ ማድረግ

አሊብኝ። እና ጠመንጃውን ቀይሬ **በዛው** ውስጥ አስቀመጥኩ፡ እንዳያመልጠኝ እርግጠኛ ለመሆን ሁለት እርምጃዎችን ወደ ኋላ ተመለስኩ፡ ከዚያም እጄን ወደ ላይ አነሳሁ፡ መራመድ ጀመርኩ፡ መራመድ። እየረፈደ ነው፡ ጨለማ፡ ንፋሱም እየነፈሰ ነው። ኦህ፡ ቅርንጫፍ እነካለሁ፡ ከዚያ እንዲህ እላለሁ፡ "ያ ነው በቃ! አይ፡ ያ አይደለም።" ኦህ፡ ይሰጣል... እርግጠኛ ያልሆነ ድምጽ እንዲሰጥ አትፍቀዱለት።

147 ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፡ ለመተው ስዘጋጅ፡ እጄ የሆነ ነገር መታ። ኦህ፡ ይገርማል! በጠፋሁ ጊዜ፡ ተገኘው። ያንን ሽቦ ያዝኩት። ጠመንጃውን ወደ ታች ጣልኩት፡ ኮፍያዬን ከጭንቅላቴ ላይ አውልቄ እዚያው ቆምኩ። "አምላኬ ሆይ፡ ከጠፉ በኋላ መገኘት፡ ምን አይነት ሲመት ነው፡" አልኩት። እንዲህ አልኩ፡ "እስከዚህ ሽቦ መጨረሻ ድረስ፡ በፍጹም እንዲጠፋ አላደርግም። በዚህ ሽቦ እያዛለሁ። በዚህ ምድር ላይ ለእኔ የምወደው ሁሉ ወደሚቀመጥበት ቦታ፡ በቀጥታ ይመራኛል። ባለቤቴ እና ልጄ፡ በፍርሃት፡ የት እንዳለሁ ሳያውቁ፡ እሳት እንዴት መፍጠር እንዳለባቸው ሳያውቁ፡ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሳያውቁ፡ እና ነፋሶች ይነፍሳሉ፡ እና ቅርንጫፎች ብቅ እያሉ ከዛፎች ይወድቃሉ።" ያንን ሽቦ ለመልቀቅ አልደፈርኩም። በምድር ላይ ውድ የሆነው ሁሉ ለእኔ ወደ ሆነበት እስኪመራኝ ድረስ ያንን ሽቦ ያዝኩት።

148 ያ በጣም አስቃቂ አጋጣሚ ነበር፡ እና መውጫዬን ለማግኘት ከባድ አጋጣሚ ነበር፡ ገና ግማሽ ላይ እንኳ አልደረስኩም። አንዴ በኃጢአት ጠፍቼ ነበረ። የሆነ ነገር ለማግኘት፡ ከቤተክርስቲያን ወደ ሌላ ቤተክርስቲያን ተንከራተትኩ። ወደ ሰባተኛው-ቀን አድቬንቲስቶች ሄድኩኝ፡ እንዲህ አሉኝ፡ "ሰንበትን ጠብቅ፡ ስጋ መብላትን አቁም።" ወደ ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን፡ ወደ መጀመሪያው የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ሄድኩ፡ እንደዚህ አለኝ፡ "ተነሥተህ በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ እንደምታምን ንገራቸው፡ እኔም አጠምቅሃለሁ፡ ያ ነው በቃ።" ምንም ነገር አልነበረም። ግን አንድ ቀን፡ በትንሽ የድንጋይ ከሰል ውስጥ፡ እጆቼን አንስቼ፡ የሆነ ነገር ያዝሁ፣ ወይም፡ አንድ ነገር፡ ያዘኝ ልበል። የሕይወት መር፡ መሪው ነበር። እና እስከዚህ ድረስ በደህና መራኝ፡ እጄን ከዚያ ሽቦ አላነሳም። እጆቼን ወደ እሱ ይዣለሁ። ሃይማኖቶች፡ ቤተ እምነቶች የፈለጉትን ያድርጉ፡ እኔ መሪውን ይዤያለው። በምድር ላይ የነበረው ሁሉ እና በሰማይ ያለው ሁሉ፡ ለእኔ ምንጊዜም ውድ ነው፡ በዚህ ሽቦ መጨረሻ ላይ ይገኛል። እስከዚህ ድረስ በደህና አመጣኝ፡ በቀረውም መንገድ እምነዋለሁ። "እርሱ መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ፡ ይመራችኋል ወደ ሁሉም ይወስዳችኋል... "

149 ጓደኞቼ፡ ዛሬ ያለሁበት ያደረሰኝ እሱ ነው። የሆንኩትን አድርጎኛል። በደስታ ላስተዋውቅችሁ እችላለሁ። እዚህ በምድር ላይ ወይም እዚያ ላይ፡ ስለማንኛውም ነገር የማውቀው ብቸኛው መሪ እሱ ነው። አደን ስሄድ መሪዬ ነው። ዓሣ ለማጥመድ ስሄድ እርሱ መሪዬ ነው። ከአንድ ሰው ጋር ሳወራ እሱ መሪዬ ነው። ስሰብክ እርሱ መሪዬ ነው። ስተኛ እርሱ መሪዬ ነው።

150 እና ልሞት ስመጣ፡ እርሱ በወንዙ ላይ ይቆማል። በመንገዱን አሻግሮ ይመራኛል። "አንተ ከእኔ ጋር ነህና፡ ክፉን አልፈራም። በትርህና ምርኩዝህ ያርሙኛል፡ ወንዙንም አሻግረው ይመሩኛል።"

እንጸልይ።

151 የሰማዩ አባት ሆይ፡ ስለሚመራኝ፡ ስለ መሪው በጣም አመሰግናለሁ። ኦህ፡ አንዳንድ ጊዜ፡ አባቴ፡ በዙሪያዬ እሱን መስማት አልችልም፡ እፈራለሁ። በወንዙ ላይ በምን ሰዓት እንደምሮጥ ስለማላውቅ ወደ እኔ እንዲቀርብ እፈልጋለሁ። አጠገቤ እንዲሆን እፈልጋለሁ። መቼም አትተወኝ፡ ጌታ ሆይ። መናገር አልችልም፡ መሰበክ አልችልም፡ ጫካ ውስጥ ማደን አልችልም፡ ውሃ ላይ ዓሣ ማጥመድ አልችልም፡ መኪናዬን መንዳት አልችልም፡ ያለ አንተ ማድረግ የምችለው ነገር የለም። አንተ መሪዬ ነህ። ዛሬ ማታ ለዚህ ጉባኤ እንዲህ ማለቴ ምን ያህል ደስተኛ ነኝ፡ በዚህ ሁሉ እንዴት እንደ መራኸኝ፡ እንዴት እንዳመጣኸኝ!

152 ባለፈው ቀን እያሰብኩ ነበር፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት፡ እዚህ መንገድ ላይ ቆሜ፡ እና ቤተሰቤ ስህተት ስለሰሩ፡ ማንም አያናግረኝም። ለአብሮነት ብቻዬን ነበርኩ። ማንም ከእኔ ጋር ምንም ማድረግ አልፈለገም። እንደዝህ አሉኝ፡ "አባቱ ህግወጥ ነው።" ጌታ ሆይ፡ ማንም እንደማያናግረኝ አየሁ። እና ሰዎችን እወዳለሁ። ግን አንድ ቀን ያንን ሸቦ ሰይዘው! አሁን ይመስለኛል፡ ጌታ ሆይ፡ ትንሽ እረፍት ለማግኘት ተንሸራትቼ ወደ ምድረ በዳ መውጣት አለብኝ። ያ ምን አደረገ? ስብዕና አይደለም፡ ትምህርት አይደለም፣ ምንም የለኝም። ግን አንተ ነበርክ፡ ጌታ ሆይ። አንተ፡ ጌታ ሆይ። ዒላማውን ዜሮ ሰጥተኸኛል፡ ትልቁን ዓሣ እንድይዝ ፈቀድክልኝ፡ ምክንያቱም ያንን ማድረግ እንደምፈልግ ታውቃለህ። አባቶችንና እናቶችን ሰጥተኸኛል። ወንድሞች እና እህቶች ሰጥተኸኛል። ጤናዬን ሰጠኸኝ። ሚስት ሰጥተኸኛል። ቤተሰብ ሰጥተኸኛል። አንተ መሪዬ ነህ፡ ጌታ ሆይ። እጅህን እንድይዝ ፍቀድልኝ፡ መቼም እንዲለቀው አትፍቀድ። አንድ እጅ ከደከመ፡ እጄን ብቻ እቀይራለሁ። እርዳኝ፡ ጌታ ሆይ።

153 ጌታ ሆይ፡ አሁን እዚህ ያለው እያንዳንዱ ሰው ያንኑን የሕይወት መሰመርን፡ ሕይወታችን የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ፡ የሕይወት ምንጭ ያግኝ። እና ሁላችንንም ወደዚያች ደስታ ወደሚገኝባት ምድር ይምራን፡ የሕይወት ድካም ያበቃና በምድር ላይ ሥራችን ይፈጸማል፡ ከዚያም በኋላ እርጅናና ደካሞች አይገኙባትም፡ ደከመኝ ሰለቸኝ አይሉም፡ ከእንግዲህ ወዲህ ልቅሶና ጸሎት የለም፡ የመሠዊያ ጥሪ አይኖርም፡ እዚያ ግን ለዘላለም ወጣት እንሆናለን፡ ህመም እና ሀዘን ከእንግዲህ አይኖሩም። ዳግመኛ ኃጢአት አይኖርም፡ በሚመጡትም ዘመናት ሁሉ በማይቋረጥ ዘላለማዊነት፡ በእግዚአብሔር ጽድቅ እንኖራለን። ሰጠን፡ አባት ሆይ።

154 እና አሁን፡ አባቴ ሆይ፡ ዛሬ ማታ እዚህ የህይወት መሰመርን ይዞ የማያውቅ ካለ፡ አሁኑኑ ያግኙ። የመራኝም መንፈስ ቅዱስ... እና በቃልህ ላይ በእጄ እያለ፡ ከልቤ መናገር እችላለሁ፡ እሱ ሁል ጊዜ ትክክል ነው። ብዙ ጊዜ ተሳስቻለሁ። እሱ ግን ልክ ነው። ከእኔ ጋር እንዲቆይ አድርገው፡ ጌታ ሆይ። ከእርሱ ጋርም እንድቆይ አድርገኝ። እና ሌሎች በዚህ ምሽት፡ እርሱን የማያውቁ፡ የማይለወጠውንም እጁን ይይዙ ዘንድ፡ በእርሱ ይመሩ።

155 እና አንድ ቀን ወደ ወንዙ እንወጣለን። በዚያ ጠዋትም፡ ጭጋጋማ ይሆናል። የጥንቱ ባህር ይጮኻል፡ የጥንቱ ዮርዳኖስ፡ ሰባሪዎቹ ይደቅቃሉ፡ ሞት ህይወትን

ከውስጣችን አንቆ ለማጣት ይተጋል። ነገር ግን፡ እግዚአብሔር፡ እኔ—እኔ አልፈራም። ከረዥም ጊዜ በፊት አስተካክያለሁና። ልክ እንደ ተዋጊ፡ የራስ ቁር፡ ማውለቅ ፈገለግሁ፡ ሽቦው የት እንደመራኝ ለማየት መንገዱን ወደ ኋላ ተመልከቱ። ያለፍኩበትን ምድረ በዳ ሁሉ፡ አሜከላንም ሁሉ፡ ያቆሰለኝን የድንጋይ ክምር ሁሉ እዩ፡ ግን መስመሩን ይዣለሁ። እንዳላችሁት፡ ገጣሚው እንዲህ ብሏል፡

ከፊሉ በውሃ፡ ከፊሉም በጎርፍ፡
አንዳንዶቹ በጥልቅ ፈተናዎች ውስጥ፡ ሁሉም ግን አለፉ
በደም።

እናም በመንገድ ላይ የጠበቀኝን፡ **ይህንን** ጥንታዊው ሰይፍ፡ ወሰጄ፡ ወደ ሰገባው መልሼ አስገባዋለሁ፡ "አባት ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት ጀልባውን ላክ፡ ወደ ቤት እመጣለሁ፡" እላለሁ። እዚያ ትሆናለህ፡ ጌታ ሆይ። ቃል ገብተሃል። አንተ አትወድቅም።

156 አሁን እዚህ ያሉትን ሁሉ ባርካቸው። ይህንን ሽቦ እንዴት እንደሚይዙ ካላወቁ እና በጭራሽ ካልነኩት፡ ወደ ላይ የተዘረጉ የተቀደሱ እጆች፡ የሚፈልጉ እጆች፡ የሚሹ እጆች፡ ወደ ልባቸውም ፍላጎት፡ ፍጹም ሰላም እና እርካታ፡ በክርስቶስ ወደ ማረፍ የሚመራቸውን የህይወት መስመር ይንኩ።

157 አንገታችንን ዝቅ አድርገን፡ እጃችን ወደ ላይ አንስተን እና እንዲህ እንላለን፡ "ፍቀድልኝ። እጄን ያዝ"? ኦህ፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

መንገዱ አስፈሪ በሆነ ጊዜ፡ ወደ ውድ ጌታ፡ እቀርባለው፡
ሕይወቴ ሊጠፋ ሲቃረብ፡
በወንዙ ላይ እቆማለሁ፡
እግሬን ምራኝ፡ እጄን ያዝ፡
እጄን ያዝ፡ ውድ ጌታ ሆይ፡ ምራኝ።

158 እንዲህ እያለ፡ እጁን የሚያነሳ ሌላ ሰው ይኖር ይሆን፡ "ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ የህይወት መስመርን መንካት እፈልጋለሁ። ክርስቶስ ኃጢአቴን ይቅር እንዳለኝ እንዲሰማኝ እፈልጋለሁ፡ ከዚህ ሰዓት ጀምሮ አዲስ ፍጥረት መሆን እፈልጋለሁ የሚል ይኖር ይሆን"? እግዚአብሔር ይባርካችሁ። "አቤቱ ልነካህ፡ ጌታ ሆይ። ራሴን እንድክድ ፍቀድልኝ፡" የሚል ሌላ ሰው ይኖር ይሆን? እግዚአብሔር ይባርክሽ እህቴ። "ጌታ ሆይ፡ በአንተ፡ ራሴን ልካድ፡ እና ላግኘው።" እግዚአብሔር ይባርካችሁ። እና እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ትክክል ነው። "ራሴን ልካድ ጌታ ሆይ። እንድረሳው ፍቀድልኝ።" እግዚአብሔር ይባርክህ ወንድሜ። "ፍቀድልኝ… " እግዚአብሔር ይባርክሽ እህቴ። "እውቀቴን ብቻ እንድክድ ፍቀድልኝ።" እግዚአብሔር ይባርክሽ እህቴ። በሰው-ሰራሽ ዘዴዎች አትታመኑ። መሪውን ተከተሉ፡ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል። "ምራኝ፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ምራኝ።" እግዚአብሔር ይባርካችሁ ከኋላ። ኦህ፡ መዳንን የሚፈልጉ፡ ብዙ እጆች ተነስተዋል። አሁን እኛ እያለን…

159 መሠዊያው እዚህ ነው ያለው፡ መሠዊያ ብላችሁ መጥራት አትችሉም፡ ምክንያቱም ሰዎች በሁሉም ቦታ ተቀምጠዋል። ግን እዚህ ነው ያለው። ጥሩ እና በደንብ ታውቃላችሁ፡ እጃችሁን ስታነሱ፡ በልባችሁ ውስጥ የሆነ ነገር ሆኖ ነው። ኢየሱስም እንድህ ኣለ፡ "ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም

ሕይወት አለው።” እንደዛ ማለታችሁ ነው? ከዚያም እዚህ ገንዳው በውኃ የተሞላ ነው። ለጥምቀት ብዙ ጊዜ ይኖረናል። እንጸልይ።

160 የሰማዩ አባታችን ሆይ፡ በዛሬ ማታ በዚህች በጎረነነ ድምፅ የተ-ሰባበረች ትንሽ መልዕክት፡ መንፈስ ቅዱስ የሆነ ቦታ መሄዱ አይቀርም። ወደታሰበው ቦታ ሄዷል፡ እና ብዙዎች፡ ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ አስራ አምስት ወይም ሃያ የሚሆኑ እጆቻቸውን አንስተዋል፡ ይህም መሪው እንደሚያስፈልጋቸው ነው። እራሳቸውን ማታለላቸውን ተገንዝበዋል። “ደህና ነኝ” ለማለት ይሞክራሉ፡ በውስጥ ሰውነታቸው ግን ደህና እንዳልሆኑ ያውቃሉ። እና ጌታ ሆይ አንተ እንድትሰማቸው ይፈልጋሉ። መሪውን ይፈልጋሉ። መመዝገብ ይፈልጋሉ። በፍፁም አትበዛባቸውም። ለዚህ ጉዞ መመዝገብ ይፈልጋሉ። ወደዚያ እንዴት እንደሚደርሱ አያውቁም። ወደዚያ እንዴት እንደሚወሰዳቸው የሚያውቅ የለም፡ አንተ ብቻ ነህ። እየመጡ ያሉት እግዚአብሔር ወዳዘጋጀው መሪ፡ ወደ መንፈስ ቅዱስ ነው። እጃቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርገዋል።

161 መንፈስ ቅዱስ እና መሪ ሆይ፡ በላያቸው ውረድ። ኃጢአትን ሁሉ ይቅር በል። በደላቸውን ይቅር በልላቸው። ዛሬ ማታ የእግዚአብሔር ጅረት በዚያ ሸቦ ውስጥ ሲፈስ ወደ ሚሰማቸው፡ ወደ ክርስቶስ አካል ውስዳቸው ይህም ወደ ዮርዳኖስ ያወርዳቸዋል፡ እና ዮርዳኖስን ማዶ ወደ ተስፋይቱ ምድር ይመራቸዋል። ከቃሉ ጀርባ ቀጥ ብለው ይከተሉ። ቃሉ እንዲህ አለ፡ “ንስሐ ግቡ፡ ከዚያም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ።” በሌላ መንገድ አይሞክሩት። የሚመራው እርሱ ነውና፡ ከቃሉ ጀርባ ይከተሉ። ያ ነው—መሪውን ለመያዝ እስክንችል ድረስ የመውጣት ደረጃ ያ ነው። ስጠን፡ ጌታ ሆይ። ያንተ ይሁኑ። እንደ ሽልማት፡ አሁን በእጅህ ናቸው፡ ማንም ሊነጥቃቸው አይችልም። እንደዳኑ ሰዎች፡ እንደምትወስዳቸው አምናለሁ። እጆቻቸውን ወደ ላይ እንዳነሱ አምናለሁ፡ የሆነ ነገር ካላናገራቸው በስተቀር በራሳቸው ማድረግ አይችሉም ነበር። መንፈስ ቅዱስ እና መሪ፡ አንተ ነህ።

162 ሰዓቱ መቃረቡን፡ ጭጋግ ወደ ምድር እየመጣ መሆኑን አይተውታል፡ ታላላቅ ሃይማኖቶች እና—እና ነገሮች አንድ ላይ ሲሆኑ፡ አብያተ ክርስቲያናት፡ አንድ ላይ ሆነው ይደራጃሉ። እና፡ አምላክ ሆይ፡ እንዴት እንደዝህ ለማለት ይሞክራሉ፡ “ልዩ ባህሪ ያለው ሁሉ እዚህ ትቶ ወደ አላስካ መሄድ አለበት።” እና እነዚህ ሁሉ የሚያስፈራሩዋቸው ነገሮች፡ ለእኛ አዲስ አይደሉም፡ ታላቁ መሪ ያንን በቃሉ መንገድ አሳይቶናል። ከዚያ አንዱን ክፍል ብቻ ነው እያለፍን ያለነው።

163 እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታ ተናግረሃቸዋል፡ እና አሁን እንደ ቃሉ ሽልማቶች ወደ አንተ ሰጥቻቸዋለሁ። በኢየሱስ ስም።

164 አሁን፡ አባት ሆይ፡ እዚህ ጠረጴዛው ላይ የተቀመጡት፡ የጸሎት መሀረብ ናቸው፡ ለታመሙ ሰዎች ነው፡ በውስጣቸው ትንሽ የፀጉር ማስያዣዎች እንኳን ተይዘዋል፡ የሆነ ትንሽ ሕፃን፡ ምናልባት፡ የሆነች እናት፡ የሆነች እህት፡ የሆነ ወንድም። አሁንም ወደ እኔ አቀርባቸዋለሁ። አሁን፡ ከጳውሎስ አካል መሀረብና መጎናጸፊያ እንደወሰዱ በመጽሐፍ ቅዱስ ተምረናል፡ ድውያንም ይፈወሱ፡ ርኩሳን መናፍስትም ከሰው ይወጡ ነበር። ጌታ ሆይ፡ ጳውሎስ ሰው እንደነበረ፡ ሰው ብቻ እንደነበረ፡ ተገንዝበናል። ነገር ግን መሀረብን የባረከው በእርሱ ላይ

የነበረው የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ነው፡ ሰዎችም በእምነታቸው እርሱ ሐዋርያህ ነው አሉ። አሁን ጳውሎስ ከእኛ ተወሰዷል፡ መሪው ግን አልተወሰደም፡ አሁንም እዚህ አለ። እና፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ እነዚህን መሀረቦች እንድትባርክ እጸልያለሁ፡ እና መሪው ወደ ቦታው ይመራቸዋል፡ ሙሉ በሙሉ ይማረካሉ።

165 አሁንም እስራኤል መሪያቸውን ተከትለው፡ ወደ ዮርዳኖስ መውረዳቸውን እንደተነገረን፡ ቀጥታ (ይልቅ) ወደ ቀይ ባህር ወረዱ፡ በግዳጅ ሽቦ ላይ ቆሙ፡ መሪውም ወደዚያ ወሰዳቸው። ምንድን? ክብሩን ለማሳየት። እናም ሁሉም ተስፋዎች ባለቁ ጊዜ፡ እግዚአብሔር በዚያ የእሳት አምድ ውስጥ ተመለከተ፡ እና አሮግቷ ሙት ባህር እንኳን ፈራች እና ወደ ኋላ ሸሸች፡ ለእስራኤልም ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲሄዱ መንገድ ተሠራ።

166 በእውነት፡ ጌታ ሆይ፡ አሁንም አንተ ያው አምላክ ነህ። እነዚህ ሰዎች ምናልባት ክርስቲያኖች ሊሆኑ ይችላሉ፡ ምናልባት እነሱ በግዴታ መንገድ ላይ ናቸው፡ ነገር ግን ሕመም ወደ አጣበባቸው ወደዚህ ጠባብ ሰፍራ መጡ። ዛሬ ማታ የኢየሱስን ደም ተመልከቱ፡ ዲያብሎስ ያንን ይፈራዋል፡ ተመልሶም ይሄዳል፡ ልጆችሽም ወደ ሰላም ቃል ኪዳን ያልፋሉ። ስጠን፡ አባት ሆይ። ከሥጋዬ ወደ እነርሱ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም እልካቸዋለሁ።

167 ይህን ጉባኤ በፊትህ አነሳዋለሁ፡ በእምነት በሰማይ ወደሚገኘው ወደሚከበረው ወደ እግዚአብሔር መሠዊያ ቱንቢ እወስዳቸዋለሁ። ለእያንዳንዱ የሕመም ፍላጎት፡ ምንም ዓይነት ችግር ያለባቸው፡ በሕይወታቸው ውስጥ በትኛውም ቦታ ላይ ችግር የሆነ፡ አምላክ ሆይ፡ አጽዳቸው፡ ያንተ አድርጋቸው። ፈውሳቸው፡ አባት ሆይ። ኢየሱስንም ከመቃብር ያስነሣው ኃይል፡ የሚሞተውን ሰውነታቸውን ሕያው በማድረግ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ያድርጋቼው። አንተን ለማገልገል ጥሩ ጤንነት እና ጥንካሬ ሰጣቸው።

168 አሰበኝ፡ ኦ አምላኬ። እኔ ባሪያህ ነኝ። ጸሎት አስፈልጎኝ ቆሜአለሁና፡ እርዳኝ። መንፈስ ቅዱስም እንዲመራንና እንዲጠቀምብን እጸልያለሁ፡ እና በመነጠቅ በአየር ላይ ስንገናኝ ኢየሱስ ክርስቶስን በክብር ምጽአቱ ፊት ለፊት እስከምንመለከትበት ቀን ድረስ ይምራን። በክርስቶስ ሰም እንጠይቃለን። አሜን።

> እሱን እወደዋለሁ፡ እኔ... (እናንተስ? )
> ቀድሞ እሱ ወደኛልና
> መዳኔንም ገዝቷል
> በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

169 አሁን፡ የተያያችሁትን እርስ በርሳችሁ ካልተዋደዳችሁ፡ ያላያችሁትን እንዴት ትወዱታላችሁ? አሁን **እወደዋለሁ** ብለን ስንዘምር፡ ለባልንጀራችን ከልብ የሆነ የፍቅር መጨባበጥ እንስጠው።

> እወደዋለው...

እግዚአብሔር ይባርክህ... ? ... እግዚአብሔር ይባርክሽ... ? ... እግዚአብሔር ይባርክህ... ? ... ወንድም ኔቪል፡ እግዚአብሔር ይባርክህ... ? ... ኧሃ-ሃህ። እግዚአብሔር ይባርክሽ... ? ...

> በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

አሁን እጆቻችንን ወደ እሱ እናንሳ።

እወደዋለው፡ እወደዋለው
ቀድሞ እሱ ወዶኛልና
መዳኔንም ገዛ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

170 ጥሩ ዝማሬ፡ አንድ መሰማት ትፈልጋላችሁ? እዚህ ኢንዲያናፖሊስ የመጣ የወንጌል መዝሙር መሪ እንዳለን ተረድቻለሁ። በካድል ተበርናክል ውስጥ እንደሚዘምር አምናለሁ። ልክ ነው? መልካም፡ ወዳጄ። ሰፍራው በካድል ተበርናክል ዘንድ ነው። ኢ ሃዋርድ ካድልን ሰንቶቻችሁ ታስታውሱታላችሁ? ኦህ፡ ይገርማል! እግዚአብሔር ውድ ነፍሱን ያሳርፍ። መዝሙሯን የወደድኩላት ሴት፡ በሰማይ ላይ እንደ አዋፋት ዝማሬ፡ በህወቴ ሲዘምሩ ከሰሚቼው ሰዎች ሁሉ የተሻለች፡ ወይዘሮ ካድል፡ ሰትዘምር፡ “ዛሬ ጠዋት ከክፍልህ ወጥተሃል፡ ጋሻ እንዲሆን፡ በመድኃኒታችን በክርሰቶሰ ሰም ለመጸለይ አሰበሃል ወይ? ”

171 እዚያ ከመንገዱ ማዶ አንድ ቀን ጠዋት፡ በትንሽ አሮጌ ባለ-ሁለት ክፍል ዳስ ውሰጥ፡ ተነሳሁ፡ ገብቼ እሳት ላቀጣጥል ፈልጌ። ምድጃው እምቢ አለ። እና ልጀምር ሞከርኩ፡ እና ንፋሱ ወርዶ፡ ነገሩን ፊቴ ላይ በቴነው። እናም ቀዝቃዛ ነበር፡ እናም ልቀዘቅዝ ነበር። እና መሬት ላይ ሁሉ ውርጭ፡ እና እኔ ባዶ እግሬን፣ ይህን ትንሽ ያረጀ የቆርቆሮ ምድጃ ለመጀመር በመሞከር ላይ፡ ትንሽ የምድጃ ቱቦ በላዩ ላይ። እና እኔ ብቻ... እኔና ሚዳ ከተጋባን ቅርብ ጊዜ ነበር። እና እየሞከርኩ ነበር፡ አሮጌው አንጨት እርጥብ ነበር እና አይቃጠልም፡ እና እዚያ ተቀምጫለሁ፡ አሰብኩ፡ “ኦህ፡ ይገርማል! እንደገና እሞክራለሁ።” ወደ ሥራ መሄድ ነበረብኝ፡ እና **ያንን** ያረጀ ምድጃ እንደዚያ ማራገብ ነበረብኝ። እናም ደረሰኩና ራዲዮውን ከፈትኩኝ፡ እሷም መዘመር ጀመረች። “ዛሬ ጠዋት ከክፍልህ ወጥተሃልን፡ ለመጸለይ አሰበሃልን፡” በቃ መሬት ላይ ወደቅኩኝ፡ “ዛሬ ዛሬ እንደ ጋሻ እንዲሆን፡ በመድኃኒታችን በክርሰቶሰ ሰም ለመጸለይ አሰበሃልን? ” ኦህ፡ ያቺን ሴት መሰማት እንዴት ደስ ይለኛል!

172 አንዳንድ ጊዜ ወንዙን ሰሻገር፡ ወይዘሮ ካድልን እዚያ ላይ ተቀምጬ እንደምሰማት አምናለሁ። ታውቃላችሁ፡ ሁልጊዜ ቀጠሮ እይዛለው። በወንዙ በዚህ በኩል፡ የማይረግፍ ዛፍ አለ፡ ታውቃላችሁ፡ የሕይወት ዛፍ፡ እና ከወንዙ ማዶ፡ ቀንና ሌሊት የመልአኩ መዘምራን፡ እዚያ ሌሊት ሰለሌል፡ ቀኑን ሙሉ ይዘምራሉ፡ አያችሁ። የሆነ ቦታ አገኝና ወደ ኋላ መልሼ አዳምጣለሁ። ወይዘሮ ካድል እዚያ ሲትዘምር እንደምሰማ አምናለሁ።

173 እግዚአብሔር ይባርክ ወንድማችን። ሰሙን ረሳሁት። ማን ነበር፡ ወንድሜ? [ያ ወንድም እንዲህ አለ፡ “ኔድ ውልማን።”—እርታዒ።] ወንድም ኔድ ውልማን አሁን ይዘምርላችኋል። ወንድም ውልማን፡ ዛሬ ማታ እዚህ በመምጣትህ ደስ ብሎኛል። [ወንድም ዋልማን **ዘ ቻፕል ኦፍ ማይ ሃርት** ብሎ ዘመረ።]

**መሪው** AMH62-1014E

(A Guide)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ ጥቅምት 14፡ 1962፡ እሁድ ማታ፡ በዩ/ኤስ/ኤ/ ጄፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና፡ ከሚገኛው ብራንሃም ተብርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቨ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጐሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡



Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org